# የግብርና ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# የግብርና ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የስልጠና ሞጁል)

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# የግብርና ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

## (የስልጠና ሞጁል)


አዘጋጆች:

ፍቃዱ ነገሳ (PhD): ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ተስፋዬ ሂርጳሳ (PhD): የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኋላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ



© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን



ህዳር 2017 ዓ.ም

# ማውጫ (Table of Contents)

ይዘቶች ........................................................................................ገጽ
ማውጫ (Table of Contents) .................... iv
አጠቃላይ የሞጁሉ መግቢያ .................... vi
የሞጁሉ አጠቃቀምና አቀራረብ .................... vii
የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ .................... ix
ተተኳር ሰልጣኞች (Target Trainees) .................... ix
አጠቃላይ ለሞጁሉ የተሰጠው ሰዓት .................... ix
ለሥልጠናው የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ .................... ix
ምዕራፍ አንድ .................... 1
የሙስና ወንጀል ምንነት .................... 1
1.1. መግቢያ .................... 1
1.2. የምእራፉ ዓላማ .................... 1
1.3. የተፈቀደው ሰዓት .................... 1
1.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች .................... 1
1.5. የሙስና ምንነት .................... 1
1.6. የሙስና ዓይነቶች (Types of corruption) .................... 3
1.8. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች .................... 9
የማጠቃለያ ጥያቄዎች .................... 16
ምዕራፍ ሁለት .................... 18
የግብርናዉ ዘርፍና ሙስና .................... 18
2.1. መግቢያ .................... 18
2.2. የምእራፉ ዓላማ .................... 18
2.3. የተፈቀደው ሰዓት .................... 18
2.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች .................... 18
2.6. የግብርናዉ ዘርፍ ባህሪ .................... 23
2.7. ግብርና ዘርፍና የሙስና ተጋላጭነቱ .................... 25
ማጠቃለያ ጥያቄዎች .................... 39
ማጠቃለያ. .................... 40
ምዕራፍ ሶስት .................... 41
ሙስና በግብርና ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት እና መከላከያ ስልቶች .................... 41

3.1. መግቢያ ..... 41

3.3. የተፈቀደው ሰዓት ..... 42

3.4. ሙስና በግብርና ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት (Impact of Corruption in Agriculture) ..... 42

**3.5. በግብርናው ዘርፍ የሚፈፀሙ ሙስና መከላከያ ስልቶች (Means of mitigating corruption in agricultural sector)** ..... 48

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች** ..... 48

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች** ..... 56

ማጠቃለያ. ..... 56

4. የ ቅድመ እና ድህረ ስልጠና ቼክ ሊስት (pre & post training Checklist) ..... 57

5. ዋቢ (References) ..... 59

# አጠቃላይ የሞጁሉ መግቢያ

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከተሰጡት ተቀዳሚ ኃላፊነቶች አንዱ ስነ-ምግባርን ማጎልበትና ሙስናን በመከላከል የግንዛቤ ስራዎችን በማከናወን ዜጎች ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የመከላከል አቅማቸውን እና ንቃተ-ህሊናቸዉን ማሳደግ ነው፡፡ ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ዓመታት የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም መጠነ ሰፊ የግንዛቤ ግንባታና ማበልፀጊያ መድረኮች እና ስልጠናዎችን ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ሲሰጥ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

ኮሚሽኑ በራሱም ሆነ በሌሎች ባለድርሻ አካላት ለሚካሄደ መሰረታዊ፣ ወቅታዊ እና አንገብጋቢ በሚባሉ የሙስና እና ብልሹ ተግባራት መከላከል አሰራሮችና ስነ-ምግባር ነክ ርዕሶች ዙሪያ ማሰልጠኛና ግንዛቤ ማጎልበቻ የሚሆኑ ሞጁሎችን አዘጋጅቷል፡፡ በዚህ መርህ መሰረት በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ እያዘጋጃቸዉ ከሚገኙ የስልጠና ርዕሶች መካከል አንዱ “በግብርና ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመከላከል” የሚዳስስ ሞጁል ነው፡፡ ይህ በግብርና ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከል ዙሪያ የተዘጋጀ ሞጁል በቀዳሚነት የመንግስት የስራ ኃሊፊዎችና ሰራተኞች በግብርና ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ በማጎልበት፣ በግብርና ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከሉ ረገድ የላቀ ኃላፊነት እንዲወጡ በምያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡

ይህንን ሞጁል ለማዘጋጀት የኢፌዲሪ ህገመንግስት፣ የሙስና ወንጀልን የሚመለከቱ ህጎች፣ በሙስናና ብልሹ አሰራሮች፣ በግብርና ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ጥናቶች እንዲሁም የዚህን ዘርፍ ሙስና መከላከል ላይ የተዘጋጁ የስልጠና ሞጁሎች፣ አለምአቀፍና አህጉር አቀፍ ስምምነቶች፣ የአገር ውስጥና የዉጭ የምርምር ጽሑፎች እና ከባለሙያዎች ጋር የተደረጉ ውይይቶችና ሌሎችም በግብአትነት ተጠቅመናል፡፡

የስልጠና ሞጁሉ ሶስት ክፍልች ሲኖሩት የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ የሙስና ጽንሰ ሀሳብ መሰረታዊ ጉዳዮችን የሚሸፍን ሆኖ ቀርቧል፡፡ በዚሁ ክፍል የሚሸፈኑት ፍሬ ሃሳቦች፤ የሙስና ምንነት፤ የሙስና ዓይነቶች (Types of corruption)፤ ዝቅተኛ ሙስና (Petty corruption)፤ ከባድ ሙስና (Grand corruption)፤ ስርዓታዊ ሙስና (systemic capture)፤ ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption)፤ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎችእና ሌሎች ትኩረት የሚሹ ቦታዎች/ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ምዕራፍ ሁለት የግብርናዉ ዘርፍና ሙስና የሚመለከት ስሆን በዚሁ ክፍል የተዳሰሱት ርዕሶች፣ የግብርናዉ ዘርፍ ባህሪ፣ ግብርና ዘርፍና

የሙስና ተጋላጭነቱ፣ የግብርናዉ ዘርፍ እሴት ሰነሰለት እና ሌሎች ትኩረት የሚሹ ቦታዎች/ሁኔታዎች ናቸው።

ምዕራፍ ሶስት በዋናነት ሙስና በግብርና ላይ የሚያስከትለዉን ጉዳቶችን እና መከላከያ ስልቶች የዳሰሰ ስሆን በዚሁ ክፍል የተዳሰሱት፣ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ፣ የአካባቢ መበላሸት፣ማህበራዊ አንድምታ (Social implications)፣ የምግብ ዋስትና ስጋቶች እና የአየር ንብረት አደጋ በዝርዝር ቀርቧል። በመጨረሻ በግብርና ዘርፍ ሙስናን የመከላከል ዘዴዎች (Means of Mitigating Corruption in Agricutlural Sector) በዝርዝር ቀርቧል። በዚህም መሰረት፣ የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን፣ የቅንነት ባህልን ማጎልበት፣ የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ፣ የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ፣ የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ፣ የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር፣ ትምህርት እና ስልጠና (Education and training)፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት ፣ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል የቀረበበት ክፍል ነው።

ሰልጣኞች በሞጁሉ ማለትም "በግብርና ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል" ሞጁል ዉስጥ የተካተቱ ጉዳዮች ላይ የዳበረ ግንዛቤ እና ዕውቀት እንዲኖራቸው እንዲሁም እርስ በእርስ ተሞክሮ መለዋወጥ የሚያስችሉ የማነቃቂያ እና መልመጃ ጥያቄዎች ተካተዋል።

በዚሁ መሰረት ሰልጣኞች መልመጃ ጥያቄዎችንና ኬዞችን በግልም ሆነ በቡድን በመሥራትና በመወያየት ልምድና ግንዛቤቸውን የሚያዳብሩበት እድል ይሰጣል ተብሎ ይታመናል።

## የሞጁሉ አጠቃቀምና አቀራረብ

ይህ የማስልጠኛ ሞጁል ሲዘጋጅ ለአሰልጣኞችና ለሰልጣኞች የሚመች እና አሳታፊ በሆነ መንገድ ማቅረብ እንዲቻል የተዘጋጀ ነው። ለዚህም ሰልጣኞች ቀደም ሲል ካላቸው እውቀትና የስራ ተሞክሮ በመነሳት እየተወያዩና እየተከራከሩ ወደ ጋራ የመግባባት ደረጃ እንዲደርሱ የተለያዩ ተግባራት፣ መልመጃዎችና ኬዞች ቀርበዋል።

ንዑስ ርዕሶች ለውይይት ከመቅረባቸው በፊት በግልና አጠገብ ለአጠገብ ያሉ ሰልጣኞች በሚቀርቡት ርዕሶች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ይገልጻሉ። አሰልጣኙ በፅንሰ-ሃሳቦች ወይም በርዕሶች ዙሪያ በምሳሌ እና በተሞክሮ በተደገፈ ገለፃ እና ማብራሪያ ይሰጣል። አሰልጣኙ የሚወያዩበት እንዱሁም በየርዕሶቹ መካከልና መጨረሻ የተቀመጡ የቡድን ወይይት ጉዳዮችና ጥያቄዎች ላይ

በመነጋገር፣ በመከራከርና ሌሎች ማረጋገጫ ሃሳቦችን በማቅረብ ግንዛያባቸውና እውቀታቸውን የሚያዳብሩበትን ሁኔታ በሚፈጥር መንገድ የተዘጋጀ ነው።

አሠልጣኙ ከሰልጠና ዓላማዎች፣ የርዕስ ይዘቶች በመነሳት አጠር ያለና ሙያዊ ገለፃና ማብራሪያ በመስጠት ጠንካራ ድምዳሜ ላይ እንደሚደርስ ይታሰባል። በዚህ ሂደት በአብዛኛው አሰልጣኙ ስልጠናውን የማመቻቸት ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል።

የሞጁሉ ይዘቶች፣ የመወያያ መልመጃዎችንና ተግባራትን ለማቅረብ የሚከተሉት ዋና ዋና ዘዴዎችን ተጠቅሟል።

**የቡድን ወይይት** (Group discussion)

የቡድን ውይይት ሰልጣኞች በተነሱ ጭብጦች ዙሪያ ካላቸው ቀደምት ልምድ ተነስተው ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ለማድረግ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው። በመሆኑም ሰልጣኞችን በትንንሽ እና በትልልቅ ቡድን በማድረግ ማወያየትና ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ማድረግ ይገባል።

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች** (Brainstorming sessions)

የአእምሮ ጓዳን ማንኳኳት ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በተቀመጡ ጥያቄዎች መሰረት ቁልፍ ለሆኑ ሃሳቦች ሰልጣኞች ከቀደምት እውቀትና ልምዳቸው ተነስተው ሃሳባቸውን እንዲገልጹ የማነሳሳት ተግባር ነው።

**ገለጻ** (Presentations)

ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ወይም ሃሳቦች ዙሪያ ሰልጣኞችን ለማገዝ በአሰልጣኞች አማካኝነት የሚሰጥ ገለፃ ወይም ማብራሪያ ነው።

**ኬዝ ጥናት** (Case studies)

የኬዝ ጥናት በተግባር በተፈጸሙና እንደምሳሌ በቀረቡ ጉዳዮች ላይ ሰልጣኞች በቡድን፣ በጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ታስቦ የቀረበ ስልት ነው። አሰልጣኞች እንደ ይዘቶቹ ሁኔታ፣እንደመለማመጃዎቹ ጠባይና እንደቀረበው ትእዛዝ ከለይ የቀረቡትን ስልቶች ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው ይጠበቃል። ይሁን እንጂ አሰልጣኞች በአማራጭነት ከቀረቡት የሥልጠና ተግባራት ወይም መልመጃዎች እና የአቀራረብ ሥልቶች ውጭ የተሻለ ዘዴ አለ ብለዉ ያመኑበትን መጠቀም ይችላሉ።

## የሞጁሉ አጠቃላይ ዓላማ

ሰልጣኞች በዚህ ሞጁል የሰፈሩትን ጉዳዮች ከሸፈኑ እና ሰልጠናዉን ካጠናቀቁ በኋላ፡- የግብርና ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመከላከልና ማስተዳደር አቅማቸውን በእውቀትና በአመለካከት በማሳደግ የተሰጣቸውን ሚናና ኃላፊነት በመረጃ ላይ በመመስረት በተቋማቸው ዉስጥ የግብርና ዘርፍ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን እንዳይከሰት ለመከላከል ያግዛቸዋል፡፡

## ተተኳር ሰልጣኞች (Target Trainees)

በግብርና ሚንስቴር እና በተጠሪ ተቋማት ስር የሚገኙ አመራርና ሰራተኞች፣

## አጠቃላይ ለሞጁሉ የተሰጠው ሰዓት

ሞጁለ የ12 ሰዓት ስልጠና ጊዜ የሚሸፈን ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡

## ለሥልጠናው የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ

- ✓ ላፕቶፕ (Laptop)
- ✓ ዳታ ፕሮጀክተር በኤልሲዲ እና ማገናኛ ኬብሎች ላፕቶፑን ከፕሮጀክተሩ ጋር ለማገናኘት
- ✓ የተንሸራታች ቻርት ማቆሚያዎች (Flipchart stands)
- ✓ የነጭ A3 ተንሸራታች ወረቀት እና የሚሠሩ የግልባጭ ገበታ እስክሪብቶች (ቢያንስ 20 ንፁህ ሉሆች ከተገለበጠው ገበታ ላይ ለመሰካት ቀዳዳ ያላቸው)
- ✓ ለአሰልጣኝ ማስታወሻዎች ትንሽ የላይኛው ጠረጴዛ (Small top table for trainer notes)
- ✓ ለተሳታፊዎች ባጅ (badge labels for participants)
- ✓ ብዕር (Pen)

# ምዕራፍ አንድ

# የሙስና ወንጀል ምንነት

## 1.1. መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀብል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው፡፡ ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምእራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ምእራፍ ነው፡፡

## 1.2. የምእራፉ ዓላማ

ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-

1. የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
2. በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤

## 1.3. የተፈቀደው ሰዓት

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4፤00 ሰዓት

## 1.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች

<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤</u>

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ፡፡

## 1.5. የሙስና ምንነት

ሙስና የእንግሊዝኛውን "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወሰደ ቃል ነው፡፡ ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም

የተባበሩት መንግሰታት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን እና የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ፣ የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመሰጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፤

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል“ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ “… የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል…” በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀለ ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል፡፡ የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ

ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎችስ መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

## 1.6. የሙስና ዓይነቶች (Types of corruption)

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሲሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption) እና ሲስተሚክ (state capture) ሙስና ተብሎ ይከፈላል፡፡

### *1.6.1. ዝቅተኛ ሙስና (Petty corruption)*

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሸከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

ዝቅተኛ ሙስና፣ በተባበሩት መንግስታት የጸረ ሙስና ኮንቬንሽን (UNCAC) መሰረት አነስተኛ ወይም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ሙስናዎችን የሚያመለክት ሲሆን በተለይም በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ቦታቸውን ለግል ጥቅም የሚውሉ ትንንሽ ባለስልጣናትን ወይም ግለሰቦችን ይመለከታል።

### 1.6.2. ከባድ *ሙስና (*Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው። ከዚህ አኳያ የተሸሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 " ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፤-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፤ኢኮኖሚ ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ ወይም የሚችሉ የሙስናንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል።

የተባበሩት መንግስታት የጸረ ሙስና ኮንቬንሽን (UNCAC) በጽሁፉ ውስጥ "ከባድ ሙስና"ን በግልፅ ባይገልጽም በጥቅሉ ግን ከፍተኛ ባለስልጣናትን የሚያሳትፍ ሙስና ወይም መጠነ ሰፊ ህገወጥ ተግባራት በማለት ይጠራዋል። ከባድ ሙስና በተለይ የህዝብ ተቋማትን ወይም አጠቃላይ የአገሪቱን ዘርፎች የሚጎዳ ነው። ኮንቬንሽኑ የሚያተኩረው እንደ ሕገወጥ ማበልጸግ፣ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ እና የመንግሥት ሀብት መመዝበር፣ የትላልቅ የሙስና ጉዳዮች የተለመዱ ነገሮች ናቸው።

### 1.6.3. ስርዓታዊ ሙስና (systemic capture)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት

የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው። ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል። ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic capture ) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው።

**የኬዝ ትንተና I**

*መመሪያ: ከታች የተገለጹትን ኬዝች በመመርመር የተፈፀሙ የሙስና ዓይነቶች እና የሙስና መገለጫዎችን ለይታችሁ ለተሳታፉዎች አቅርቡ።--------------------------------------------------*

*------------------------------------------------------------------------------------------*

**ኬዝ 1. የአፈር ማዳበሪያ ሙስና**

ሽመልስ አስረዲን በተባለው ግለሰብ ላይ በቀረበ የክስ መዝገብ እንደተመላከተው የዋጋ ግምቱ ከ1 ሚሊየን ብር በላይ የሆነ 450 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በተሽከርካሪ በመጫን በግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ስም የተዘጋጀ ሀሰተኛ የወጪ ደረሰኝ ሰነዶችን በመጠቀም መነሻውን አዲስ አበባ በማድረግ ወደ አማራ ክልል በማጓጓዝ ላይ እያለ በሰሜን ሸዋ ዞን ፍቼ ከተማ ዲዳ ሄጦ በተባለ ቦታ ላይ በፀጥታ አካላት ፍተሻ በቁጥጥር ስር ውሏል። ምንጭ፣(ፀረ-ሙስና ጋዜጣ ቅፅ 01 ቁጥር 25)። **Source:** https://www.fanabc.com/archives/253760

**ኬዝ 2. ለኤክስፖርት የተዘጋጀ ቡና ሙስና**

የመከላከያ አባል የሆነዉ ሻንበል ከበደ መልካሙ፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አባል የሆነው በረከት ተስፋዬ እና የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት አባል የሆነው ወንድሙ ታደሰን ጨምሮ አጠቃላይ 11 ግለሰቦች በጥቅም በመመሳጠር በመጋቢት ወር 2015 ዓ/ም በተለያዩ ቀናት ኤክስፖርት የሚደረግ ቡና ወደ አዲስ አበባ እንደሚመጣ በስልክ በመደዋወልና መረጃ በመለዋወጥ በመነጋገር ተሽከርካሪውን አስቁመው ለመውሰድ በመስማማት ዝግጅት አደረጉ። በዚህ መልኩ ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ከሲዳማ ክልል ዳዬ ቦንሳ ዳዬ ከተማ እና ዳሌ ወረዳ ማንቼ ቀበሌ መነሻቸውን ያደረጉ ኤክስፖርት ቡና የጫኑ ሁለት የጭነት ተሽከርካሪዎችን ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ በመኪና በመከተል በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 06 አካባቢ ተሽከርካሪዎቹ ላይ መንገድ በመዝጋት እና በማስቆም ሾፌሮችንና ረዳቶችን ማአስወረዱ። ሾፌሮችንና ረዳቶችን በማስፈራራት እና በቁጥጥር ስር እንደዋሉ በመግለጽም ቡናውን የጫኑ ተሽከርካሪዎችን በሌላ አሽከርካሪ በመውሰድ በተከራየበት መጋዘን ውስጥ ቡናውን አራግፈው መኪናውን ጉለሌ ክ/ከተማ

ሩፋኤል አካባቢ አቁመው ሄዱ፡፡ በዚህ መልኩ ከ338 ኩንታል በላይ የታጠበን ቡና ሸጠዉ ለግል ጥቅማቸዉ አዋሉ፡፡ ምንጭ፣(ፀረ-ሙስና ጋዜጣ ቅፅ 01 ቁጥር 16)፡፡

### 1.6.4. ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዱሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

### ኬዝ 3. የበመሬት ባለቤትነት ሙስናየ

በአዲስ አበባ በአንዱ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር የቦታ ርክክብና ክትትል ቡድን መሪ የሆኑት አቶ ለማ፤ የሊዝ ማስተላለፍ ባለሙያ የሆኑት አቶ ያሲን፥ እና ሌላኛዋ የሊዝ ማስተላለፍ ባለሙያ የሆነቸዉ ወይዘሮ ሜሮን የግል ተበዳይ ሐምሌ 3 ቀን 2015 ዓ.ም በሊዝ የገዙትን ቦታ ለመረከብ ሲመላለሱ ከቆዩ በኋላ የግንባታ ማስጀመሪያ ፈቃድ እንዲራዘምላቸው ለመጠየቅ አገልግሎት ፈልገው ነበር ወደ ክፍለ ከተማው አስተዳደር የሄዱት፡፡ ይሁን እንጂ እነዝህ ሶስቱ ግለሰቦች ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ሲጠበቅባቸው ቀጠሮ በማብዛት ሲያመላልሷቸው ቆይተዉ እና ጉዳዩን ለመፈፀም ገንዘብ ይጠይቁአቸዋል፡፡ በሊዝ የተገዛው ቦታ መንገድ ዳር በመሆኑ እኛ ለምንፈፅምልዎት ጉዳይ የሚከፍሉን ገንዘብ ይጨምራል የሚል መደራደሪያ ሃሳብ በማቅረብ ተጠርጣሪዎቹ 3 ሚሊዮን ብር ጠይቀው ነበር ሆኖም በመጨረሻም ወደ 1 ሚሊዮን 5 መቶ ሺህ ብር ዝቅ አደረጉላቸዉ፡፡ ከተጠየቀው ገንዘብ ውስጥ 1 ሚሊዮን 2 መቶ ሺህ ብሩ የሊዝ ማስተላለፍ ባለሙያው በሆነችዉ እህት የባንክ ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ የቀረዉን 300 ሺህ ብር በጥሬ ገንዘብ ተቀብለዋል፡፡

## 1.7. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ ሆነ ወንጀል። የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ፣ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ። የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፤

### *1.7.1. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት*

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ። በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ። የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ። ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል።

### *1.7.2. የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት*

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል ። ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል። ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል። ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል። በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል።

### *1.7.3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም*

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት

ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው፡፡ ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

### *1.7.4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር*

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

“የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም” የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

### *1.7.5. ድንበር ተሻጋሪነቱ*

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ

ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆኑን ሊጊሊግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

## 1.8. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

### *1.8.1. በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)*

*ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡*

### *1.8.2. ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)*

*ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡*

### *1.8.3. የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)*

*ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡*

### *1.8.4. አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)*

*ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡*

### *1.8.5. የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)*

*ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦ በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤*

*አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤ በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡*

### *1.8.6. አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)*

*ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦*

*የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡*

### *1.8.7. በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)*

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም፦

የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### *1.8.8. በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)*

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤ በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### *1.8.9. በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)*

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦

ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረከብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.10. ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.11. ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡ በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

### 1.8.12. ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.13. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤

ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

### *1.8.14. የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)*

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ፣ ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### *1.8.15. መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)*

ማንኛዉም ሰው  የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤ አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### *1.8.16. መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)*

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ  እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.17. ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡ በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡

### 1.8.18. ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.19. ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.8.20. በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኂላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.8.21. በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ

ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል፡፡

ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### *1.8.22. በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)*

*ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡*

### *1.8.23. ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)*

*ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡*

### *1.8.24. ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)*

*ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ፡፡*

### *1.8.25. በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)*

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. "ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት" በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤
2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. "ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል" ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

**ማጠቃለያ**

*በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡*

# ምዕራፍ ሁለት

## የግብርናዉ ዘርፍና ሙስና

### 2.1. መግቢያ

በዚህ ክፍል ዉስጥ ሰልጣኞች የግብርና ዘርፍ ልዩ ባሃሪያትና የሙስናን ቁርኝት ያጠናሉ፡፡ ሙስና እንዴት በግብርናዉ ዘርፍ የእሴት ሰንሰለት ዉስጥ ሊያጋጥም እንደሚችል ይገነዘባሉ፡፡ በዘርፍ የእሴት ሰንሰለት ዉስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮችን በመለየት ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያስችላል፡፡ በዚህ ክፍል ዉስጥ የሚቀርቡትን ትምህርቶች ለማብራራት የተጠቅምናቸዉ ኬዞች እዉነተኞች ቢሆኑም ኬዞቹ ላይ የቀረቡት የሰዎች ስምና የድርጅቶች ስም የተለወጡ መሆናቸዉን እገልጻለን፡፡

### 2.2. የምእራፉ ዓላማ

**ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-**

- የግብርናዉ ዘረፍ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያለዉን ሚና ይዘረዝራሉ፤
- ሙስና በዘርፉ ላይ ያለዉን ተጽእኖ ይዘረዝራሉ፤
- ሙስና በዘረፉ የእሴት ሰንሰለቶች ዉስጥ ምን እንደሚመስል ያብራራለ፣

### 2.3. የተፈቀደው ሰዓት

ይህን ማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4:00 ሰዓት

### 2.4. የማነቃቂያ ጥያቄዎች

**<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤</u>**

1. ለግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት በተሰጣቸዉ ኃላፊነት አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ምንድን ናቸው?
2. ሙስና የዘርፉን ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ (የስራ እድል ከመፍጠር አካያ፤ ከደኀዉ መህበረሰብ ጋር ካለዉ ግንኙነት አንጻር እና ለሌሎች ዘርፎ እድገት ካለዉ አስተዋጽኦ አንጻር) እንዴት ሊያቀጭጭ ይችላል?

## 2.5. የግብርና ዘርፍ እና ዓላማዎች

በግብርናዉ ዘርፍ የሚታዩትን ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን እንዲሁም ሙስና በዘርፉ ላይ የሚያመጣዉን ተጽኖ እና የመከላከያ ዘዴዉን በዝርዝር ከማየታችን በፊት የግብርና ዘርፍ ምንነት እና ለዘርፉ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ባጭሩ ከአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 20 በመነሳት ማቅረብ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ግብርና አፈርን የማልማት፣ ሰብል የማብቀል እና የእንስሳት እርባታ ጥበብ እና ሳይንስ ነው፡፡ የእጽዋትና የእንስሳት ተዋጽኦዎችን ማዘጋጀት እና ለገበያ ማከፋፈልን ያጠቃልላል (Rutledge et al. 2011)፡፡ ሰፊ በሆነው ግብርና ዘርፍ ውስጥ የመሬት ባለቤትነት እና ይዞታ፣ የብድር አቅርቦት፣ የአቅርቦት ጥራት፣ የውሃ ድልድል፣ ግብይት እና የግብርና ንግድ (agribusinesses) ልማት በሙስና የመጠቃት እድል አላቸው (Fink, 2002)፡፡ ዘርፉ በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ ግንዛቤን ለማግኘት አንዱ ዘዴ የግብርና እሴት ሰንሰለቶችን መረዳት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ እውቀት በተለያዩ የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸውን የሙስና አደጋዎች እና የፀረ-ሙስና እርምጃዎችን ለመለየት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ አብዛኞዎቹ የግብርና እሴት ሰንሰለቶች አምስት ደረጃዎች አሏቸው፡፡ እነዚህም ግብአት፣ ምርት፣ ማቀነባበር (processing) እና ማሸግ፣ ማከማቸት (storage) እና ስርጭት እና የመጨረሻ ግብይት (end markets) ናቸው፡፡

የግብርና እና የደን ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና የሕግ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ለማጠናከርም የዕለት ደራሽ ድጋፍ እና የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡

የግብርና ምርት ስርጭትና ግብይትን በተመለከተም በሰብል ምርት፣ በእንስሳትና ዓሳ እና የተፈጥሮ ሃብት ልማት ግብዓቶች ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በገበያ የሚቀርብ ማናቸውንም የሰብል ምርት፣ እንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል

ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል። ከግብርና ኢንቨስትመንት እና ከግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አንፃር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ መደራጀታቸውን ያረጋገጣል፤ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት አማራጮችንና እምቅ አቅሞችን ይለያል፣ የኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፣ በዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋገጣል። እንዲሁም በግብርና ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ከፋይናንስ ሥርዓት ጋር ተያይዞ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች እና በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ዘርፍ ተዋንያን ተደራሽ የሆነ የግብርናና ገጠር ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ የግብርና የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ያደርጋል።

ከአገልግሎት አሰጣጥ እና ከቴክኖሎጂ ማስፋፋት አንፃር፣ የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግበዓት እና አገልግሎት ምዝገባና ቁጥጥር ይዘረጋል፣ የምርት ጥራት፣ ግብርናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል። እንዲሁም የሰብል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የምርት ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የግብርና ኤክስቴንሽን ምክር አገለግሎት፣ የቴክኖሎጂ እና አመራረት ስልቶች አቅርቦት እንዲስፋፋና አጠቃቀሙም እንዲያድግ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል። የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምን በተመለከተ ለገጠር መሬት አስተዳደርና ለተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ዘላቂ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍም ይሰጣል። እንዲሁም በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በገበያ የሚመራ የእንስሳት ሃብት ልማት፣ ውሃን ማዕከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የግጦሽ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ልማት አጠቃቀም ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል። በተጨማሪም የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል።

በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 20 መሰረት ከላይ የተጠቀሱት ስልጣንና ሀላፊነት ለግብርና ሚኒስቴርና ለተጠሪ ተቋማቱ ቢሰጥም በአፈጻጸማቸዉ ላይ ግን ከ 2011 እስከ 2020 ያለዉ የኢትዮጵያ የግብርና ሴክተር ፖሊሲ እና እንቨስትመንት ፈሬምዎርክ ግምገማ እንደሚሳየዉ

የሚከተሉት ክፍተቶችና የአፈጻጸም ችግሮች ይታይባቸዋል፡፡ እነዚህ በግምገማዉ የተለዩት ክፍተቶች በሴክተሩ ዉሰጥ ለሚፈጠረዉ የመልካም አስተዳደር ችግርና ለሙስና መጋለጥ ምክኒያት ሊሆን ይችላል፡፡

## 1. በሴክተሩ እና በተጠሪ ተቋማት መካክል የሚታዩ የትስስር እና የቅንጅቶች ክፍተቶች

- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና በተጠሪ ተቋማት መካከል በቂ የሆነ ግንኙነት አለመኖር፤
- ደካማ የምርምር-የኤክስቴንሽን እና-የገበሬዎች ትስስር፤ እና ከግሉ ዘርፍ ጋር የለዉ የግንኙነት እና ትብብር ደካማ መሆን፣
- በፌደራል እና በክልል መንግስታት እንዲሁም በለጋሽ ድርጅቶች መካከል የልማት እቅድ ቅንጅት አለመኖር ፣
- የአነስተኛ፣ መካከለኛና ትላልቅ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ የኃላፊነት ወሰን በደንብ ግልጽ ሆኖ ቢቀመጥም የጥገናውን ሃላፊነት እና የውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ሚና በግልጽ አለመቀመጥ፤
- በምርጥ ዘር አቅርቦት ውስጥ ያሉ ተቋማዊ አደረጃጀቶች በተሻለ ሁኔታ የተቀናጁ እና በግልጽ የተብራሩ ኃላፊነቶችን ለዕፅዋትን እርባታ፤ መሠረታዊ የዘር አቅርቦት እና ዘር ማባዛት፤ ማከፋፈል/ ግብይት፤ የጥራት ቁጥጥር/ የምስክር ወረቀት እና ዋጋ ወዘተ... አለመኖሩ፡፡

## 2. በሴክተሩ የሚታዩ የስትራቴጂ ክፍተቶች

- የግብርና ግብይት እና እሴት መጨመር በዋናነት መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ በነጋዴዎች በኩል ይካሄዳል፡፡ ደካማ የግብይት አገልግሎቶች እና መገልገያዎች በገጠር አካባቢዎች ያለው መጓጓዣ ለግብርና ንግድ ሥራ ትልቅ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ በዋና ዋና የግብርና ምርቶች እሴት ሰንሰለቶች ላይ የግብርና ንግድ ትስስርን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡
- በማዳበሪያ ምርት እና አቅርቦት ሰንሰለት ላይ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያበረታታ ስትራቴጂ መከለስ አለበት፡፡
- በደካማ የቅድመ-መኸር አሠራር እና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ከ15-20 ከመቶ አካባቢ ዓመታዊ ምርት ብክነት ሲያጋጥም፤ ከተሰበሰበ በኋላ ደግሞ እስከ 30 በመቶ

የሚደርሰው ምርት በአግባቡ ባለማጓጓዝ፣ ባለማከማቸት፣ በተባይ መከላከል ችግር ወዘተ ይባክናል፡፡

- በእንስሳት ላይ ያሉ ቁልፍ ምርታማነት ችግሮችን ለመፍታት የተሻሻለ የእንስሳት ንኡስ ዘርፍ ስትራቴጂ ያስፈልጋል፤ የግጦሽ መሬት እጥረት ባለባቸው ደጋማ አካባቢዎችም ሆነ በቆላማ አካባቢዎች በእርሻ መሬት መራቆት ምክንያት የእንስሳት መኖ በከፍተኛ ሁኔታ ችግር እየሆነ መጥቱል፡፡

3. በሴክተሩ የሚታዩ የፖሊሲ ክፍተቶች፡

- በእንስሳት ሀብት ልማት ፖሊሲ ላይ የትኩረት ጉድለት አለ፤ የእንስሳት እርባታ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ተቀርጿል፣ ነገር ግን ይህ ለእንስሳት ጤና እና አመጋገብ እነዲሁም ለተዛማጅ ጉዳዮች ትኩረት የሰጠ አይደለም፡፡
- ከፍተኛ ጥራት ያለው ዘር በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረቡ ለተሻሻለ ግብርና ምርታማነት ወሳኝ ነው፡፡ በሁሉም የዘር አቅርቦት ሰንሰለት ደረጃዎች ከአዳራቢ ዘር እስከ ለንግድ የተረጋገጠ ዘር ድረስ ወሳኝ የሆነ የፖሊሲ ማሻሻያ መደረግ እንዳለበት ይታያል፡፡ የዘር ፖሊሲን እና የምስክር ወረቀት ስርዓቶችን ወጥ ማድረግ በክልሎች መካከል ለሚደረግ የዘር ግብይት አስፈላጊ ሆኖ ይታያል፡፡
- የፋይናንስ አገልግሎት አለማገኘት የአነስተኛ ባለሀብቶችን እና የታዳጊ አርሶ አደሮችን የተሻሻሉ የግብርና አሰራሮችን የመጠቀም አቅም እየገደበ ነው፡፡

**መለመጃ 2.1.**

**የግብርናዉን ዘረፍ ሥልጣንና ተግባራት ካጠናችሁ በኃላ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተወያዩ**

- ለግብርናው ዘርፍ (ለግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት) የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ምንምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተወያዩ ባቸዉ፡፡
- ለግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት በተሰጣቸዉ ኃላፊነት አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት ተወያዩ፡፡

## 2.6. የግብርናዉ ዘርፍ ባህሪ

ግብርና አፈርን የማልማት፣ ሰብል የማብቀል እና የእንስሳት እርባታ ጥበብ እና ሳይንስ ነው። የእጽዋትና የእንስሳት ተዋጽኦዎችን ማዘጋጀት እና ለገበያ ማከፋፈልን ያጠቃልላል (Rutledge et al. 2011)። በዚህ ሰፊ ፍቺ መሰረት እንደ ሁኔታው የተለያዩ ሂደቶችን እና ተዋናዮችን ከትናንሽ ከእጅ ወደ-አፍ እርሻ (small-scale subsistence farming) እስከ ትላልቅ የንግድ እርሻዎች ያቀፉ ከመሆናቸው አንፃር የግብርና ዘርፎች ተፈጥሮ እና አይነት ሊለያዩ ይችላሉ (Dastrup, 2019)። በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ግብርና ከፍተኛውን የህዝብ ቁጥር እና በአብዛኛው በኢኮኖሚ በጣም ደካማ የሆነዉን የህዝብ ክፍል ይጠቀማል፤ በእነዚህ አገሮች ውስጥ ያሉ እርሻዎች ትንሽ ናቸው። በአፍሪካ ለምሳሌ ከ 90% በላይ እርሻዎች በአነስተኛ መሬት ባለቤቶች እጅ ናቸው። አርሶ አደሮች ጉቦ የሚከፍሉት ከዝቅተኛ ገቢያቸው አንጻር በመቶኛ ከፍ ያለ በመሆኑ ከእጅ ወደ አፍ የሆነዉ ኑሮዋቸዉ በተነጻጻሪነት ክፉኛ በሙስና ይጎዳል።

ይህ ዘርፍ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ እና ለኢንዱስትሪው ዘርፍ መሰረታዊ ጥሬ ዕቃዎችን በማቅረብ የኢኮኖሚ መሰረት ስለሚሆን በግብርናው ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና ከፍተኛ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል። አብዛኛው ሕዝብ ግብርና ዋና መተዳደሪያ በሆነባቸው ገጠራማ አካባቢዎች በሚኖርባቸው በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ተጽእኖው የበለጠ ከባድ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም በእነዚህ አገሮች ግብርና በዋናነት የሚከናወነዉ በጥቃቅንና አነስተኛ እና መሬት በሌላቸው ገበሬዎች ሲሆን ባጠቃላይ የአቅም እና የካፒታል ችግር ያለባቸው እና በፖለቲካ ዉስጥ የተሳትፎ ድምጽ የሌላቸው ገበሬዎች ናቸው (Brankov and Tanjević, 2013) ።

ግብርና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ትልቁ ዘርፍ ሲሆን ከ 50% በላይ የሀገር ውስጥ ጥቅል ምርት እና ከ 85% በላይ ለስራ ለደረሰዉ የሰው ኃይል የስራ እድል ፈጥሩዋል (MEDaC,1999)። ሶስት አራተኛው የኢትዮጵያ የማኑፋክቸሪንግ ምርት ምግብ፣ መጠጦች፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ትምባሆ፣ ቆዳ፣ ማተሚያ ወረቀት እና ብረት ያልሆኑ ማዕድናት ናቸዉ (በፍቃዱ እና በረሃኑ፣ 2000)። ምግብ ትልቁን ድርሻ ይይዛል (ወደ 30% የሚጠጋ)፤ ከዚያም ጨርቃ ጨርቅ እና መጠጦች ይህም ከ 20% በላይ እና ከ 10% በላይ ይሸፍናል ተብሎ ይገመታል። ማኑፋክቸሪንግ በኢትዮጲያ ለአበዛኛዉ ጥሬ ዕቃዎች በግብርና ላይ የተመሰረተ ነው፤ ስለዚህም የግብርና ዕድገት በማኑፋክቸሪንግ  እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋጾ ያመጣል ተብሎ ይገመታል።

እንደ ኦሮሚያ ቱዴይ ጋዜጣ ዘገባ (OT, 2023), ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል አርሶ አደሩ በተለያዩ እርከኖች ያለውን የሙስና ጫና በመሸከም በከፍተኛ ተጋላጭነት ላይ የሚያገኙ ናቸው። 40

በመቶ ለሚሆነው የኢትዮጵያ አጠቃላይ ምርት አስተዋጽኦ ያደረገው የገበሬዎች የግብርና ውጤቶች መሆናቸውን ልብ ሊባል ይገባል። ሆኖም አርሶ አደሮች በህብረተሰቡ ውስጥ እጅግ በጣም ደሃ እና መሰረታዊ አገልግሎቶች የሌላቸው ናቸው።

**መለመጃ 2.2.**

የግብርና ዘረፍ አስተዋጽኦና አጠቃላይ ባሂሪ ካጠናችሁ በኃላ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተወያዩ

- ሙስና የዘርፉን ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ (የስራ እድል ከመፍጠር አካያ፣ ከደንዉ መህበረሰብ ጋር ካለዉ ግንኙነት አንጻር እና ለሌሎች ዘርፎች እድገት ካለዉ አስተዋጽኦ አንጻር) እንዴት ሊያቀጭጨዉ እንደሚቺል ይወያዩ።
- መንግስት በዘርፉ የሚታየዉን ሙስና ለመዋጋት የሳየዉ ትኩረት ምን ይመስላል?
- ከሚከተለው ሥዕል የተረዳችሁትን አስረዳ




**ምስል 1.** የግብርና ዘርፍ ሙስና

## 2.7. ግብርና ዘርፍና የሙስና ተጋላጭነቱ

የፌድራል ስነምግባረና ጸረ-ሙስና ኮምሽን በሚያዘጋጀዉ ጋዜጣ ላይ የግብርና የዘርፉ ባለሞያዎች በሰጡት አስተያየት እንደተገለጸዉ፤ በኢትዮጵያ የግብርናው ዘርፍ ለሙስና እና ለመልካም አስተዳደር ችግር የሚያጋልጡ ጉዳዮች ብሎ ሲዘረዝር፤

1. የህብረት ስራ ማህበራት አሰራር፤
2. ከአፈር ማዳበሪያ ግዥ፥ የዋጋ መናር፥ የስርጫት ሂደት፥ ከወደብ በሚፈለገው ፍጥነት ባለመነሳቱ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሁኔታ፣
3. የቡና ምርት አቅርቦትና ኤክስፖርት አስተዳደር፣
4. የአበባ ልማት ኢንቨስትመንት መሬት አጠቃቀም ፤የኬሚካልና ሌሎች አገልግሎቶች፣
5. የእርሻ መሬት ለኢንቨስትመንት የሚሰጥበትና የመሬቱ አጠቃቀም፣
6. የፕሮግራምና ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አፈጻፀም፣
7. በመስኖ ግድቦች አስተዳደር ዙሪያ የሚገኙ ህጎች እንዲሁም ሃላፊነትና የስልጣን ክፍፍል መሆናቸውን ተጠቅሱዋል::

ሰፊ በሆነው ግብርና ዘርፍ ውስጥ የመሬት ባለቤትነት እና ይዞታ፣ የብድር አቅርቦት፣ የአቅርቦት ጥራት፣ የውሃ ድልድል፣ ግብይት እና የግብርና ንግድ (agribusinesses) ልማት በሙስና የመጠቃት እድል አላቸው (Fink, 2002):: በተመሳሳየ ሁኔታ እንደ Anik et al. 2013 እይታ በግብርናው ዘርፍ የሙስና ስጋቶች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፤

1. በግብርና ግብዓቶች ላይ የሚፈጸም ሙስና (ልክ እንደ ማዳበሪያ ወይም ዘር ያሉ በድጎማ የሚሸጡ ግባቶች) እና ለመስኖ ፓምፕ ባለቤቶች ጉቦ መስጠት
2. የግዜ ብክነትና እና የመጓጓዣ ወጪዎች ዋጋ
3. በመንግስት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ላይ የሚስተዋለው ሙስና (አርሶ አደሩ መንግስት ሊያቀርበው የሚገባቸውን ግብአቶች አያገኝም)::

ዘርፉ በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ ግንዛቤን ለማግኘት አንዱ ዘዴ የግብርና እሴት ሰንሰለቶችን መረዳት ነው:: ይህ ዓይነቱ እውቀት በተለያዩ የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸውን የሙስና አደጋዎች እና የፀረ-ሙስና እርምጃዎችን ለመለየት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል:: በእያንዳንዱ አውድ ውስጥ የግብርናውን የእሴት ሰንሰለት ትንተና ተገቢ የሙስና አደጋዎችን እና የመቀነስ ስልቶችን ለመቅረጽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል::

በግብርና ውስጥ የእሴት ሰንሰለት ማለት በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ እሴት የሚጨመርበት መሠረታዊ የግብርና ምርትን ከእርሻ ወደ መጨረሻው ፍጆታ የሚያመጡ ተዋናዮችን እና እንቅስቃሴዎችን ያሳያል። የእሴት ሰንሰለት ቀጥ ያለ ማገናኛ (vertical integration) ወይም በተለያዩ ገለልተኛ የንግድ ድርጅቶች መካከል ያለው አውታረመረብ ሲሆን ማቀነባበርን፣ ማሸግን፣ ማከማቻን፣ መጓጓዣን እና ስርጭትን ሊያካትት ይችላል (Westlake 2005) ። በተጨማሪም ከሰንሰለቱ ውጭ ላሉት ተዋናዮች ድጋፍ ሰጪ ኤጀንሲዎች፤ እንደ የምርምር ድርጅቶች፣ የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ ያሉ ሲሆን እነዚህ ሁሉ የእሴት ሰንሰለቱ በተወሰነ አውድ ይነኩታል (Farm Radio International, 2013)።

### *2.7.1. የግብርናዉ ዘርፍ እሴት ሰንሰለት*

አብዛኛዎቹ የግብርና እሴት ሰንሰለቶች አምስት ደረጃዎች ይኖራቸዋል፡ ግብአት፣ ምርት፣ ሂደት እና ማሸግ፣ ማከማቻ እና ስርጭት እና የመጨረሻ ገበያዎች። የግብርና መሰረታዊ የእሴት ሰንሰለት መዋቅርን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከተሉት የሙስና አደጋዎች በየደረጃዉቹ ሊለዩ ይችላሉ፡

#### *2.7.1.1. የግብዓት የእሴት ሰንሰለት/Input stage*

የእሴት ሰንሰለቱ የመጀመሪያ የሆነው የግብአት ደረጃ የግብርናውን ሂደት ለመጀመር አስፈላጊ ተዋናዮችን እና ሂደቶችን ያካትታል። ይህም እንደ መስኖ፣ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የጉልበት ስራ፣ የገንዘብ ድጋፍ/አገልግሎት (ድጎማ እና የእርሻ ብድር) ፣ ፍቃድ፣ ሰርተፍኬት፣ ወዘተ የመሳሰሉ ከመሬት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል (Cucagna and Goldsmith 2017) ። እያንዳንዳቸው እነዚህ ጉዳዮች ለሙስና አደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ።

#### *2.7.1.2. መሬት (Land)*

መሬት ውድ ሃብት ሲሆን በመሬት ይዞታ፣ በመሬት ባለቤትነት መብት፣ በህገ-ወጥ የመሬት ወረራ እና በመሳሰሉት ለሙስና የተጋለጠ ነው። ከዓለም አቀፍ የድርጅት ICAR እና ግሎባል ዊትነስ የተገኘ ሪፖርት እንደ ሚያሳየዉ ማያንማር፣ ታንዛኒያ እና ላይቤሪያ ባሉ አገሮች ውስጥ ያለ አካባቢዉ ማህበረሰቦች የመሬት ዝውውሮች (land transfers) ፈቃድ እና ምደባዎች መደረጋቸውን ይጠቅሳል (Schutter, 2016)። እንዲሁም በአለም ደረጃ በፍጥነት እያደገ የመጣው የሰፋፊ መሬቶች የግብርና ልማት የአገር ተወላጆች መሬቶች (Indigenous lands) ውስጥ ዘልቆ መግባቱን ቀጥሏል (UN, 2021) ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2019 ለዚህ ተግባር ተብሎ በአማዞን ላይ የተደረገው የደን ጭፍጨፋ ካለፉት 11 ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። የደን

ቃጠሎን በተመለከተም፣ የግብርና ባለሙያዎች ሆን ብለው መሬታቸውን ለግብርና ንግድ ሥራ ለመክፈት ያደረጉት ሙከራ እንደሆነ የአገር ተወላጆች እና ሌሎችም ጠቁመዋል (UN, 2021; Teixeira, 2019)፡፡

ከዚህም በላይ ከገጠራማ ስፍራ አከባቢ የሚገኙ አነስተኛ አምራቾች ከመሬት ይዞታና ከይዞታ ጋር የተያያዘ ሙስና ሊያጋጥማቸው ስለሚችል ይህም የምግብ ዋስትናቸውንና ምርታማነታቸውን እንዳያሻሽሉ እንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡ በግብርናው ዘርፍ ያለው ሙስና የሚያሳድረው ተጽዕኖ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ዉስጥ ባሉት የትናንሽ መሬት ባለቤቶች ላይ እየከፋ መጥተዋል ምክኒያቱም ብዙውን ጊዜ እነዚህ የማህበረሰቡ ክፍሎች መጀመሪየዉኑ እጅግ በጣም ድሃ የሆኑ ስለ ሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሃገራተ እና በእስያ፣ 80% የሚሆነው የእርሻ መሬት አነስተኛ ይዞታ ባላቸዉ ገበሬዎች እጅ የሚተዳደር ሲሆን እስከ 80% የሚሆነውን የምግብ አቅርቦት በእነዚያ አከባቢዎች የሚሸፍኑት እነሱ ናቸዉ (Transparency International 2019)፡፡

እንደ FAO, (2012b) ጥናት መሠረት በኢትዮጵያ ሙስና ከሚፈጸምባቸዉ ቁልፍ ቦታዎች አንዱ የመሬት ድልድል ወይም ክፍፍል ነው፡፡ በገጠር አንዳንድ ቦታዎች ላይ ባለሥልጣናቱ “የሕዝብ መሬት” ተብለዉ የተለዩትን ስፍራዎች “የመንግሥት መሬት” በሚለዉ ስያሜ ስር አካተዉታል፡፡ አንዳንድ ባለሥልጣኖች የመሬት ምዝበራን ተግባራዊ ለማድረግ “ሕዝባዊ ዓላማን” እንደምክንያት ይጠቀማሉ፡፡ አንዳንድ ሥነምግባር በጎደላቸዉ ባለሥልጣኖች መሬትን ለሥራ አስፈጻሚዎች ለመስጠት በመሬት ቅርምት ላይ ተሰማርተዋል፤ ይህ በወረዳ ደረጃ እየተፈፀመ ሲሆን በቀበሌ ደረጃ በተመረጡት ኮሚቴ አባላት በተመሳሳይ ሁኔታ እየተፈጸመ ነው፡፡ ከፍተኛ መጠን ያለው የተዘረፈ መሬት ለግል ፍላጊዎች ይተላለፋል፡፡ የአነስተኛ ይዞታዎችን መዝረፍ እና ማዛወር የአበባ እርሻዎችን፣ ባዮፊውልን እና ሰፋፊ የንግድ እርሻዎችን ተጠቃሚ አድርጓል (FAO, 2012b)፡፡

እንደ FAO, (2012b) ጥናት የገጠር መሬት ወደ ማዘጋጃ ቤት የሚካለልባቸዉ የገጠር ባለይዞታዎች በመካስ ላይ ችግሮች እያጋጠሙ እንደሆነ ገልጿል፡፡ ምንም እንኳን ሕጎቹ ለካሳ ክፍያ ቢደነግጉም ለካሳ ክፍያ ኃላፊነትን የሚወስደዉ አካል ግልጽ አይደለም፡፡ ይህ ግልጽነት የጎደለው አሰራር መሬታቸው ወደ ከተማ የተካለለባቸዉ የገጠር ነዋሪዎች ካሳ የማያገኙበት ሁኔታዎች እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡

በኢትዮጵያ የመሬት ውዝግቦች ከመደበኛ የፍርድ ቤት ስርዓት ቢያንስ 50 በመቶውን ሊሸፍኑ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ አንድ ዳኛ ምስክርነት በፍርድ ቤት ከቀረቡት 4,000 ክሶች ውስጥ

3,000 የሚሆኑት ከመሬት ጋር የተገናኙ መሆናቸውን ተናግረዋል (FAO፣ 2012 ለ)። ከዚህም በላይ በአሁኑ ወቅት በሃገሪቱ የሚፈጸሙ አብዛኞቹ ወንጀሎች እንደ የንብረት ቃጠሎና እና ግድያ የመሳሰሉ ወንጀሎች ከመሬት ጋር የተያያዙ ናቸው ሲሉ ዳኛው ተናግረዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች ከመሬት ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች መጠን በጣም በፍጥነት እየጨመረ ስለመጣ ባለሥልጣናቱ የመሬት የምስክር ወረቀት መስጠት አቁመዋል። በርካታ የግጭት አፈታት አማራጮች ቢኖሩም፣ የመረጃ ልውውጥ አነስተኛ መሆን እና የመድረክ እድሎች ባለመኖሩ መደበኛው አሰራር የመሬትን አለመግባባቶች ለመፍታት ውጤታማ ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችን ለማግኘት ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃል። ይህ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ላልተፈቱ የጉዳዮች ጫና አስተዋፅዖ ያደርጋል እና ሰዎች ብዙም ግልፅ ያልሆኑ እና ፍትሃዊ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን እንዲያስቡ ያስገድዳቸዋል፤ ወይም ጥሩ ፍርድ ለማግኘት ብልሹ መንገዶችን እንዲፈልጉ ያስገድዳቸዋል (FAO፣ 2012 ለ)።

**የኬዝ ትንተና II**

***መመሪያ***፤ በቡድን በመሆን ኬዙን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ሃሳቦች ላይ ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለተሳታፉዎች አቅርቡ።

- ባላችሁበት ወረዳና ዞን ዉስጥ ከኬዙ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጉደዮች ምን ያህል ይፈጠራሉ?
- እንደዚህ ላሉ ዘረፋዎች ትልቁን ሚና የሚጫወቱት እነማን ናቸዉ? (ባንኮች፣ በየደረጃዉ ያሉ የእንቨሰትምንት ቢሮ ኃላፊዎች፤ደላሎች ወይስ ሌሎች)
- በዚህ መንገድ የሚፈጸሙትን የመሬት ዘረፋ ለማቀነስ በምን መንገድ መስራት ይሻላል?
- ክአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ የቀሰማችሁትን ልምድ ያብራሩ

**ኬዝ 4. የመሬት ግዥ ሙስና**

በአሪ ዞን በቅባት እህል ዘርፍ የኢንቨስትመንት መሬት ለመረከብ በረካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚል ስያሜ የሚንቀሳቀሰው ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ መሃመድ ሞላ ለኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ካፒታል 30 በመቶ ማለትም 32 ሚሊዮን 246 ሺህ 340 ብር እንዲሁም ከባንክ ብድር 70 በመቶ ማለትም 75 ሚሊዮን 246 ሺህ 460 ብር በጠቅላላ 107 ሚሊዮን 492 ሺህ 800 ካፒታል ማሟላት ይጠበቅባቸዉ ነበር። በቀድሞ የደቡብ ኦሞ ዞን ካቢኔ ማህበሩ የጠየቀው 10 ሺህ ሄክታር ቢሆንም ባቀረበው ካፒታል 400 ሄክታር እንዲሰጣቸው ውሳኔ ተላልፎ ለቀድሞ የደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጭምር መረጃው

እንዲደርስ መደረጉን የአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ ገልጽዋል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች አቶ መሃመድ  በወቅቱ የሚጠበቅበትን አሟልቶ ሳይረከብ ዘግይቶ በአሁን ወቅት መሬቱ ወደ ልማት መግባት እንዳለበት አዲሱ የአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ ውሳኔ በተላለፉ አቶ መሃመድ መሬቱን ለመረከብ ሲል ከአዲስ አበባ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጎፋ ካምፕ ቅርንጫፍ የድርሻውን 30 በመቶውን ቆጥቢያለሁ በሚል 48 ሚሊዮን 650 ሺህ ብር የባንክ ስቴትመንት ለአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ አቅርበዋል፡፡ በረካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አስኪያጅ ያቀረበውን የባንክ ስቴትመንት ትክክለኛ ነቱን ለማረጋገጥ መምሪያው በአቅራቢያ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ህጋዊ ደብዳቤ ይፅፋል፡፡ ንግድ ባንኩም ይህንን መነሻ በማድረግ ሲያጣራ በድርጅቱ አካውንት የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን አለመኖሩን ያረጋግጣል፡፡ በዚህም አቶ መሃመድ የባንክ ስቴትመንት አመጣሁ ወዳለው አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃው እንዲደርስ ሲደረግ ባንኩም በግለሰቡ የተከፈተ አካውንት መኖሩንና በአካውንቱ ገንዘብ አለመኖሩን ዳግም ያረጋግጣል፡፡ በዚህ ብቻ ሳያበቃ ግለሰቡ ከአዲስ አበባ ከተጠቀሰው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጎፋ ካምፕ ስቴትመንት ተሰጥቶኛል ብሎ ያቀረበው ከባንኩ ያልተሰጠ ከመሆኑም ባለፈ ሐሰተኛ ሰነድ መሆኑም ጭምር ይረጋገጣል፡፡ ምንጭ፡ ፀረ ሙስና ጋዜጣ፣ ቅፅ 01 ቁጥር 19፡፡

### 2.7.1.3. የእርሻ አቅርቦቶች (Seed, fertilizer)

በመንግስት ድጎማዎች እና በድጎማ ብድር አሰጣጥ ላይ፣ በመንግስት ኮንትራቶች ወይም ለእርሻ አቅርቦቶች ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ሙስናዎቸ የዘርፉ ሌሎች አደጋዎች ናቸው (Zúñiga 2018)፡፡ እንደ ዘርና ማዳበሪያን የመሳሰሉ የግብርና ግብአቶች ላይም ተደጋጋሚ የማጭበርበር ድርጊቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በቅርቡ በህንድ ወደ 66 ሚሊዮን ዶላር አካባቢ የሚገመት ከ23,000 ኩንታል በላይ የድጎማ ማዳበሪያ በውሸት ሽያጭ (fictitious sale) ከመንግስት መጋዘን ወጥቶ ወደ ጥቁር ገበያ በእጥፍ ዋጋ መዘዋወሩን የሚገልጽ ዘገባ ወጥቷል (Misra 2020)፡፡

በናይጄሪያ ዉስጥ ትልቁ የገጠር ሥራ ምንጭ በሆነዉ በግብርናው ዘርፍ ሙስና ትልቅ ተግዳሮት ነው (Godson-Ibeji et al. 2016) ፡፡ የናይጄሪያ መንግስት የማዳበሪያ እና የዘር አቅርቦት አገልግሎት ሁልጊዜ ለትክክለኛ ገበሬዎች የማይደርስ ሲሆን፣ ይህም በሰብል ዘላቂ ምርት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፤ ብድርን የሚቆጣጠሩ ፖለቲከኞች ገንዘብን ለመዝረፍ እድሎችን ይፈጥራሉ (Godson-Ibeji et al. 2016)፡፡ በላይቤሪያ የግብርና ሚኒስትር ጄኒን ሚሊ ኩፐር እና ምክትሎቿዋ የግብርና ኮንትራቶችን የሰጡበት መንገድ እንዲመረመረ ሆኑዋል (RFI 2022)፡፡

በማላዊ፣ ተመጣጣኝ የግብአት ፕሮግራም (Affordable Inputs Program/AIP) የምግብ ዋስትናን ለማሻሻል እና ድህነትን ለመቀነስ አነስተኛ ገበሬዎችን ላይ በማተኮር ማዳበሪያ እና ዘርን ያካተቱ ፓኬጆች ላይ ድጎማ በማድረግ ትሰራልች። ምንም እንኳን መርሃ ግብሩ የአርሶ አደሩን ወጪ በመቀነሱ ረገድ የተሳካለት ቢሆንም፣ አንዳንድ አፈፃፀም ችግሮች ለሙስና ዳርጓቸዋል ለምሳሌ በሻጭ ወኪሎች በኩል፣ ድጎማ የተደረገበትን ማዳበሪያ ለቸርቻሪ በመሸጥ ወይም ለግብአት የሚሆን ተጨማሪ ገንዘብ ከገበሬው እንዲወስዱ ጠይቀዋል፤በፕሮግራሙ ላይ የገበሬዎችን ግንዛቤ ባሰባሰበው ዘገባ ላይ አንድ ቃለ መጠይቅ የተደረገለት ሴት "ሴቶች ሰውነታቸውን የግብርና ግብዓት ለማግኘት እየተጠቀሙበት ነዉ" ብላለች (Ragasa et al. 2022)።

እንደ ኦሮሚያ ቱዴይ ጋዜጣ ዘገባ በ2015 ክረምት የማዳበሪያ የችርቻሮ ዋጋ በኩንታል ወደ 5000 ብር የሚጠጋ ሲሆን ካ2014ቱ ክረምት በ1000 ብር በላይ ዋጋዉ  ጭማሬ አሳይቷል። በዚህ ምክንያት አንዳንድ አርሶ አደሮች ለማዳበሪያ የሚሆን ገንዘብ ማሰባሰብ ባለመቻላቸው እንደ የመጨረሻ አማራጭ የወሰዱት ያለ ማዳበሪያ ሰብል መዝራትን ነበር፤ ይህም ምርቱን በጣም ስለሚቀንስ አነስተኛ ትርፋማ አማራጭ ነው፤ አንዳንዶች የእርሻ ቦታቸውን በርካሽ አከራይተው ነበር። አንዳንድ አርሶ አደሮች ደግሞ የእርሻ ቦታቸውን በከፊል ለሌላ አርሶ አደርች ለመሸጥ የተገደዱበት ሁኔታ እንዳለ ሪፖርቱ ያሳያል። ሪፖርቱ እደሚለዉ አንዳንድ የእርሻ መሬቶች ያለ ሰብል ሳይዘሩ የቀሩም አሉ፤ በመሆኑም ገበሬዎች በግብርና ድጎማ መልክ ከፍተኛ የህይወት ድጋፍ ሊደረግላቸዉ ይገባል። ቢያንስ ከውጭ የሚገቡ አስፈላጊ የግብርና ግብአቶች እንደ ማዳበሪያና ፀረ አረም ኬሚካልች ለገበሬዉ ከዉጪ በሚገቡበት ዋጋ ቢተላለፍ መልካም ነዉ።

የኦሮሚያ ቱደይ ጋዜጣ ወሳኝ ጥያቄዎችም አሉት፤

- እንደ ማዳበሪያ ያሉ የግብርና ግብአቶች በእርሻ ምርቱ ላይ እሴት የሚጨምሩበት በመሆናቸው አርሶ አደሩ ላይ ለምን የችርቻሮ ዋጋ ተጣለበት?
- ማዳበሪያ አስገብተው ለገበሬዎች ለማከፋፈል ፍቃድ የተሰጣቸው የግል ነጋዴዎች ጉዳይ ምንድን ነዉ?
- አርሶ አደሮችን በማደህየት ከማዳበሪያ ብዙ ትርፍ እያገኙ ያሉት እነማን ናቸው?
- እንደ ሲሚንቶ እና የምግብ ዘይት አከፋፋዬች ከላይ በተጠቀሱት የማዳበሪያ አስመጪዎች የማዳበሪያ ገበያም የሙስና ዘዴው አካል ሊሆን ይችል ይሆን?

ማዳበሪያ ማከፋፈያ ማዕከል ኃላፊዎች ለገበሬዉ የማዳበሪያ ከረጢቶችን ለመጫን እና ለማራገፍ "ለሠራተኞቹ ድጎማ" በሚል እስከ 500 ብር በኩንታል በግልጽ ይጠይቃሉ። በእርግጥ ይህ

ከሙስና ዝርፊያዎች አንዱ ነው፤ ነገር ግን አርሶ አደሮች ይህ ከላይ የወጣ ህጋዊ መመሪያ እንደሆነ እና ሌላ አማራጭ እንደሌለው ይነገራቸዋል፤ ለእርሻ ወቅቱ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ማዳበሪያ ለማግኘት ከጊዜ ወደ ጊዜ እጥረት እና ውድ እየሆነ የመጣ አስፈላጊ ምርት ሆኖአል፡፡

የጋዜጣዉ ሪፖረት የተመለከተው ሌላዉ ጉዳዩ የህብረት ስራ ማህበራት የአሰራር ስርዓት ለሙስና ተጋላጭነቱ፣ በዋጋ ንረት እና በማዳበሪያ ስርጭት ላይ የሚታዩ ችግሮች እና ከውጭ የሚገቡ ማዳበሪያዎችን ወደቦች ላይ በወቅቱ አለማንሳት ነው፡፡

በአጠቃላይ የግብርና ምርቶች አቅርቦትና ኤክስፖርት አስተዳደር፣ የአበባ ልማትና የኢንቨስትመንት መሬት አጠቃቀም፣ የግብርና መሬት ለኢንቨስትመንት የማቅረብ ልምድ፣ የግብርና ፕሮጀክት አስተዳደርና ትግበራ፣ የመስኖ ግድብ ሕጎችና ተጠያቂነት ጉዳዮች ለሙስና የተጋለጡ ናቸው፡፡

**የኬዝ ትንተና III**

***መመርያ፡ ከዚህ በታች የቀረቡትን ሁለት ኬዞችን በሚገባ በማጤን በሚከተሉት ነጥቡች ላይ ተወያዩባቸዉ፡፡***

- በነዚህ ሁለት ኬዞች ዉስጥ ያልተጠቀሱ በገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት ዉስጥ የሚታዩ (የተለመዱ) የስነ ምግባር ጉለቶችን ያበራሩ
- የህብረት ስራ ማህበራት እና የህገወጥ የማዳበሪያ ነጋዴዎች ግንኙነት ምን ሊሆን ይችላልን?
- ለሙስና የተጋለጡ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበሮች የገበሬዉን ምርታማነትን እና ኑሮ የሚጎዱበትን ሁኔታ ያብራሩ
- የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራትን የሙስና ተጋላጭነት እንዴት መቀነስ ይቻላል ይላሉ?

**ኬዝ 5. ምርቶችን ለግል ጥቅም**

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን የአባቦ የገበሬ ህብረት ስራ ማህበር ሰራተኛ የሆኑት ቱፋ ጫላ፣ ለሊሳ ረፊሳ እና ቶኩማ ረጋሳ ጓደኛሞች ሲሆኑ፤ አቶ ቱፋ ጫላ በህብረት ስራ ማህበሩ ውስጥ ገንዘብ ያዥ ሆኖ ሲሰራ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ 10 ሚሊየን 482 ሺህ 131 ብር ከ15 ሳንቲም የሆነ ገንዘብ አጉድለዋል፡፡ ለሊሳ ረፊሳ ደግሞ የህብረት ስራ ማህበሩ መጋዘን ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ 42 ኩንታል ማዳበሪያ፣ አምስት ኩንታል በቆሎ፣ 125 ኩንታል ነጭ ሽንኩርትና ሌሎች ምርቶችን

ባጠቃላይ የዋጋ ግምታቸው 2 ሚሊየን 441 ሺህ 34 ብር ከ34 ሳንቲም የሆኑ ምርቶችን ለግል ጥቅማቸዉ እንዲውል አድርገዋል። ቶኩማ ረጋሳ ደግሞ ከቀሩት ከሁለት ጓደኞሞቹ ጋር በመሆን በማህበሩ ስም ስምንት ሀሰተኛ የገቢ ደረሰኞችን በማሳተምና በመጠቀም 305 ሺህ 287 ብር ከ56 ሳንቲም ገቢ በሀሰተኛ ደረሰኝ በመሰብሰብ ለግል ጥቅም እንዲውል አድርገዋል። ምንጭ፤ፀረ ሙስና ጋዜጣ፣ ቅፅ 01 ቁጥር 21።

### ኬዝ 6. በግብርና ማሽኖች ላይ ሙስና

በሰንዳፋ ከተማ ጅሬኛ የተሰኘ የገበሬ ህብረት ሥራ ማህበር ከ31 ሚሊየን ብር በላይ ገንዘብ እንዲመዘበር አድርገዋል የተባሉ ተከሳሾች እስከ 14 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና በገንዘብ ተቀጡ። በችሎቱ የግራ ቀኝ ማስረጃዎችን መርምሮ የቅጣት ውሳኔውን ያሳለፈው የኦሮሚያ ክልል የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ወንጀል ችሎት ነው። የኦሮሚያ ክልል ፍትሕ ቢሮ የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ የጅሬኛ የገበሬ ህብረት ስራ ማህበር የቦርድ ሊቀ-መንበር ቶላ ፍሮምሳ፣ የማህበሩ ገንዘብ ያዢ ኩማ ቶሌራ እና የማህበሩ የሂሳብ ባለሙያ ከበደ ጫላ ጨምሮ በ10 ተከሳሾች ላይ የሙስና ወንጀልን ለመከላከል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9 ንዑስ ቁጥር 2 እና በዚሁ አዋጅ ስር በአንቀጽ 13 ንዑስ ቁጥር 2 እና ንዑስ ቁጥር 3 ስር የተመላከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል በማለት ዝርዝር ክስ አቅርቦባቸው ነበር። ተከሳሾቹ በጅሬኛ የገበሬ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ከጥር 23 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 23 ቀን 2010 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት በተለያዩ የሥራ ድርሻዎች ሲሰሩ ለገበሬው የተለያዩ ስራ ማከናወኛ የትራንስፖርት አገልግሎት በሚል ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጥ ከ20 ሚሊየን ብር በላይ ለ2 የግል ድርጅቶች ክፍያ እንዲከፈል በማድረግ በማህበሩ ላይ ጉዳት ማድረሳቸው በክሱ ተጠቅሷል። በሌላኛው ክስ ደግሞ ምንም አይነት የባንክ ደረሰኝ ባልቀረበበት ሁኔታ ላይ የገቢ መመዝገቢያ ላይ በመመዝገብ ብቻ የገቢ ደረሰኝ በመቁረጥ 10 ሚሊየን ብር ለማህበሩ ገቢ ሳይሆን እንዲመዘበር ተደርጓል። ምንጭ፤(ፀረ ሙስና ጋዜጣ፣ ቅፅ 01 ቁጥር 18)።

#### *2.7.1.4. ውሃ*

ውሃ በግብአት ደረጃ ላይ ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ነው። እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ በህንድ ውስጥ የመስኖ አስተዳደር ስርዓቶችን የተመለከተ ዝርዝር ጥናት በዘርፉ ያለውን በርካታ የተዋረድ ደረጃዎችን ያካተተ የሙስና ስርዓት ባህሪ አጉልቶ አሳይቷል። የመስኖ መሠረተ ልማትን የሚገነቡ እና ስራው ካለቀም በኋላ የሚቆጣጠሩ ተቋራጮች በአስተዳደር ኃላፊነት ላይ ለተሰማሩ መሐንዲሶች ጉቦ መክፈል ነበረባቸው። ተቋራጮቹም በተራቸው ደረጃቸውን ያልጠበቁ አገልግሎቶች በማቅረብ

አትራፊ ሆነዋል። መሬታቸው በመደበኛ መስኖ ያልተካተቱት አርሶ አደሮች ህገወጥ የውሃ አቅርቦት ለማግኘት ጉቦ እንዲከፍሉ ተደርገዋል። አጠቃላይ ስርዓቱ በአቀባዊ (vertically) የተቀናጀ ሲሆን ከሙስና የሚገኘው ገቢ ከአስተዳደር እስከ ፖለቲካ ደረጃ ድረስ በሰንሰለት የተዋቀረ ነበር። ተመሳሳይ የኪራይ ሰብሳቢነት ዘይቤዎች በባንግላዲሽ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ኔፓል፣ ፊሊፒንስ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይላንድ እና ዩናይትድ ስቴትስ ታይተዋል (Tacconi and Williams, 2020)።

**መልመጃ 2.3.**

- በኢትዮጵያ ከመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታና አስተዳደር ጋር የተያያዙ የስነምግባር ችግሮች ያብራሩ።
- ችግሮቹን ለመቅረፍ ምን ሊደረግ ይገባል ይላሉ?ይወያዩበት

### *2.7.2. ከምርት እስከ መጨረሻው የገበያ ሰንሰለት*

#### *2.7.2.1. የምርት ደረጃ (Production stage)*

ቀጣዩ የእሴት ሰንሰለት የምርት ደረጃ ነው። እንደ የእርሻ አሰራር እንዲሁም የሰብል ተፈጥሮና አይነት ይህ ደረጃ ነጠላ የእርሻ ክፍሎችን፣ የኅብረት ስራ ማህበራትን፣ ሰፋፊ እርሻዎችን፣ ወዘተ ሊያካትት ይችላል። ሰፋፊ እርሻዎች ውስጥ አንድ ነጠላ የሰብል ዝርያን (monoculture) የማምረት አካሄድ ብዙውን ጊዜ በሙስና የታጀበ ነው። ለምሳሌ በዓለም ላይ ትልቁን የፓልም ዘይት በማምረት ላይ የምትገኘው ኢንዶኔዢያ የዘንባባ እርሻን ለማልማት ሰፊ የተፈጥሮ ደኖችን መንጥራለች። አብዛኛው ይህ ሂደት የሚቀጣጠለው ያለ የአካባቢ ማህበረሰቦች ተሳትፎ በግል ኩባንያዎች እና በመንግስት ኤጀንሲዎች መካከል በሚደረጉ ግልጽ ባልሆኑ ስምምነቶች ነው (Van Hagen, 2021)።

የሙስና አመለካከቶች ለግብርና ምርት ወሳኝ በሆኑ የደንና የአፈር የጥበቃ ተግባራት ላይ ገበሬዎች እንዳይሳተፉ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ጥናት እንደሚያሳየው ከሙስና አመለካከቶች ጋር በተያያዘ በኬንያ ማእከላዊ ሀይላንድ በተደረገ የአፈር ጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኮሚቴዎች ውስጥ የገበሬውን ተሳትፎ በማዳከም ረገድ ሚናዉ ከፍያለ ነበር።

#### *2.7.2.2. የማቀነባበር እና የማሸጊያ ደረጃ/Processing and packaging stage*

የግብርና ሥራውን (agribusiness) የማቀነባበር፣ የማሸግ እና የማከፋፈያ ደረጃ ውስጥ እንደ የትራንስፖርት ፈቃድ አሰጣጥ፣ ማከማቻ፣ ጥሬ/ያልተጠናቀቀ የግብርና ምርት ትክክለኛ ሂደት

የመሳሰሉት ለበርካታ የሙስና አደጋዎች የተጋለጡ ናቸው (Fink 2002)። “ደላሎች” (“Middlemen”) ከገበሬዎች የእርሻ ምርቶችን እጅግ በወረደ ዋጋ ገዝተው ለሸማቾች ወይም ለሁለተኛ ደረጃ አቀናባሪዎች (processers) “በተጋነነ ዋጋ” ሲሸጡ ይስተዋላል። ትንንሽ አምራቾችም ያመረቱትን ምርት (በተለይ በቀላሉ የሚበላሹ (perishable) ምርቶችን) ለማከማቸት እና ለመያዝ ምንም አይነት አቅም/ሃብት የላቸውም (Oguoma et al., 2010)። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የገበሬዎችን ከደላሎች እና ከገዢዎች ጋር የመደራደር አቅም ይገድባል። በአለምአቀፍ ደረጃ በእርሻ ምርት ሰንሰለት ውስጥ እኩል ያልሆነ የሃይል ስርጭት ስጋት እንዳለ እና ገበሬዎች በተለይ በእነዚህ የኃይል ግንኙነቶች ውስጥ የተጎዱ መሆናቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ (Malak-Rawlikowska et al., 2019)።

### *2.7.2.3. የማከማቻ እና ስርጭት ደረጃ/Storage and distribution stage*

ከላይ በተጠቀሰ ደረጃዎች ከተጠቀሱት አደጋዎች በተጨማሪ ስርቆትና ምዝበራ የግብርና ምርቶችን በማከማቸትና በማከፋፈል ረገድ የተለመዱ ችግሮች ናቸው። ለአብነት ያህል፣ በቻይና መንግሥታዊ ኢንተርፕራይዝ የእህል ማከማቻ ተቋማት የሊያኦኒንግ እና ጂሊን ግዛቶች የማከማቻ ሥራ አስኪያጆች ለእህል ነጋዴዎች አዲስ የተሰበሰበ የእህል ዋጋ ለአሮጌ እህል ዋጋ በማስከፈል የህዝብን ሀብት አላግባብ እየዘረፉ እና እየመዘበሩ ነው። በተጨማሪም በግንኙነቶች ላይ የሚሰሩ የድጋፍ ስርዓቶች፣ የእህል ማከማቻ ክፍሎችን ግዥን ይወስናሉ። ስለዚህ ለሕዝብ አከፋፋዮች ለመሸጥ ግንኙነት የሌላቸው የአካባቢው ገበሬዎች ብዙውን ጊዜ ለግል ነጋዴዎች በቅናሽ ዋጋ መሸጥ አለባቸው (ዳንኒንግ 2015)። በተለይም በኢትዮጵያ ሌብነትና የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ጉቦና ኪራይ ሰብሳቢነት፣ በድጎማ የሚደረጉ ሰብሎችን ማዛባት፣ ማጭበርበር፣ የተጋነነ ኮንትራት እና የፖለቲካ ደጋፊነት በዚህ ደረጃ የሚተገበሩ ዋና ዋና የሙስና ዓይነቶች ናቸው።

### *2.7.2.4. የሸማቾች ገበያዎችን/End markets*

የግብርና እሴት ሰንሰለቶች ብዙውን ጊዜ ውስብስብ እና ግልጽ ያልሆኑ ናቸው፣ በተለይም ትላልቅ ዓለም አቀፍ ተዋናዮችን ሲያካትት (Transparency International 2019)። እ.ኤ.አ. በ 2013 የተፈጸመዉ የፈረስ ሥጋ ቅሌት ጉዳይ ይህንን ነጥብ ያስረዳል፤ ሮማኒያን ለቆ የሚወጣው ስጋ ፈረስ ተብሎ ተለጥፎ ሳለ፣ ወደ ፈረንሳይ የመጨረሻ መድረሻው ሲደርስ የበሬ ሥጋ የሚል መለያ ተሰጥቷል። የተደራጀ ወንጀል እና የሙስና ሪፖርት አቀራረብ ፕሮጀክት (Organized Crime and Corruption Reporting Project/OCCRP) ባደረገው ምርመራ መሠረት ፒንግ-

ፖንጅ ስጋው ለማስተላለፍ የሚሆን ሰፊ የወረቀት ሥራ ከሮማኒያ ወደ ኔዘርላንድስ፣ ከዚያም ወደ ቆፕሮስ ሲጻጻፍ እነደነበር አግኝተዋል (Transparency International 2019፣ Puiuleț et al. 2013)። በዚህ ቅሌት ውስጥ የተሳተፉት ኩባንያዎችም ግልፅ ያልሆኑ ሲሆን ወሳኝ ባለቤቶቹን እና ተሳታፊዎችን በማያሳይ መንገድ ተዋቅሯል (Global Witness 2013)። አንዳንድ ጊዜ በምግብ እና በግብርና ምርቶች ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች በሙስና የተዘፈቁ ኔትወርኮች ምክንያት ከህግ ገደብ ውጪ ሊሰሩ ይችላሉ (Transparency International 2019)። በግብርና ምርቶች ላይ የተሰማሩ የሸቀጦች ነጋዴዎች በዚህ ረገድ ጎልተው ይታያሉ፤ ክፍሉ በሞኖፖል የተያዘው ከ75% እስከ 90% የሚሆነውን የአለም የእህል ንግድ በሚቆጣጠሩት በአራት ዋና ነጋዴዎች ነው (Lawrence 2011; Baines et al. 2021)።

የግብርና ምርት ነጋዴዎች ደካማ አስተዳደር፣ የተቋማት፣የህግ የበላይነት እና የመንግስት ተጠያቂነት ውስንነት ባለባቸው አከባቢዉች ውስጥ እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል። ዘርፉ "እንዲሁም ግልጽ ያልሆነ" እና ደካማ ደንቦች እንዲሁም በቂ ያልሆነ ግልጽነት እና የተጠያቂነት ደረጃዎች የማይታዩበት ነዉ (ቻይን 2016; Baines et al. 2021)።

እንደ ኦሮሚያ ቱዴይ ጋዜጣ ዘገባ በ2015 በኦሮሚያ ክልል የአንድ ኩንታል ስንዴ ዋጋ 3200 ብር እንዲሆን የተወሰነ ሲሆን፤ በሥራ ላይ ያለው ዕቅድ የአገር ውስጥ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከገበሬዎች  በዚህ ዋጋ ገዝተው ለላኪዎች ከ6000 ብር በላይ በኩንታል ተሸጧል። ጥያቄው እንዲህ ካለው ትልቅ የትርፍ ህዳት ተጠቃሚው ማን ነው? በታሪክ አጋጣሚ የዋጋ አወሳሰንና የገበያ ሞኖፖሊ በደርግ ዘመን የነበረውን የኢትዮጵያ እህል ግብይት ኮርፖሬሽን የገበሬውን የነፃ ገበያ ተጠቃሚነት ያሳጣበትን ሁኔታ ያስታውሳል።

**መልመጃ 2.4.**

በእሴት ሰንሰለቱ ዉሰጥ ያሉትን ሁለቱን ደረጃዎች ማለትም (የምርት እና የማቀነባበርና ማሸግ) ከተማራችሁ በኃላ፤ በሚከተሉት ነጥቡች ላይ ተወያዩ፤

- በሀገራች ነባራዊ ሁኔታ በምርት የእሴት ሰንሰለት ላይ በተለይ በሰፋፊ እረሸዎች ሊያጋጥም የሚችለዉ የመልካም ስነምግባር ቸግሮችን ይዘርዝሩ
- ደላሎች እና ነጋዴዎች በተለይም በአትክልት እና ፍራፍሬ ምረቶችን (ከገበሬዉ ሲገዙ፣ ሲያከማቹና ለሸማች ሲሸጡ) ሊያጋጥም የሚችለዉ የመልካም ስነምግባር ቸግሮችን ይዘርዝሩ

- የግብርና ምርቶች ከተመረቱ በኃላ የሽማች ገቢያ እስኪደርስ ባለዉ ሰንሰለት ዉስጥ ያሉትን ተሳታፊዎች ብዛትና የተጠቃሚነት ሁኔታ የብራሩ

### *2.7.3. ሌሎች ትኩረት የሚሹ ቦታዎች/ሁኔታዎች*

በግብርናዉ ዘርፍ ሙስናን ለመዋጋት ወይም ለመመርመር የእሴት ሰንሰለቱን መከተል አንድ አካሄድ ቢሆንም፤ ዉስብስብ ከሆነዉ የሙስና በሃሪ አንጻር በተለየ መንገድ መመልከት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በዘርፉ የሚፈጸሙ ግዢዉች፣ በሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ላይ እና በሚንስቴሩ እና በተጠሪ ተቃሞች ዉሰጥ የሚታዩ የኦዲት ግኝቶች እና ሌሎች የተጋላጭነት ሁኔታዎችን መመርመር ጠቃሚ ይሆናል፡፡

#### *2.7.3.1. ግዢ*

የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2015 በግብርናዉ ዘርፍ ላይ ባደረገው የዳሰሳ ጥናት የግብርና ሚንስቴር ለሙስና ተጋላጭ ከሚያደርጉ አሠራሮች ጋር እየታገለ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከአንድ ድርጅት ብቻ በተሰበሰበ ፕሮፎርማ ደረሰኝ፤ በተቋማቱ በርካታ ግዢዎች መፈፀማቸውም ታውቋል፡፡ የክፍያ መዘግየት፣ የፕሮጀክቶች ሂደት ሳይረጋገጥ ክፍያ መፈጸም፣ የሚገዛው ንብረት መኖሩን ሳያረጋግጡ ግዢ መፈጸም፣ የማዳበሪያ ስርጭት መዘግየትን በተመለከተ የተሳሳተ መረጃ ለህብረተሰቡ ማሰራጨት፤ እነዚህ ሁሉ የዘርፉ የሙስና ስጋት መገለጫዎች ናቸው ተብሏል፡፡

ለምሳሌ ያህል በሚንሰቴሩ

- ስድስት ሚሊዮን ብር ያልታቀደ ግዢ እና
- ከአንድ አቅራቢ ቢቻ ግማሽ ቢሊዮን ብር እና 270 ሺህ ዶላር የሚገመት የዕቃ ጊዢ መከናወኑን ተረጋግጣል፤
- የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ከሆነው ተቋም አንዱ፤ የ73 ሚሊዮን ብር ግዥና ሌላ የ32 ሚሊዮን ብር ግዥ ያለፕሮ ፎርማ ደረሰኝ ግዥ ፈጽሟል፡፡
- አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የግዥ ዕቅድ እንዲሁም የግዥ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ግምገማ እንደሚያከናውኑ ቢገልጹም በማስረጃ ሊረጋገጥ አልቻለም፡፡ ይህም ግልፅነት እና ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል፡፡

- በዘርፉ ተቋማት በርካታ የፕሮፎርማ ግዢዎች፣ ከአንድ አቅራቢ ተደጋጋሚ ግዥዎች እንዲሁም ያለዕቅድ የሚፈፀሙ ግዥዎች መከናወናቸው መንግስትን ለአላስፈላጊ ተጨማሪ ወጪዎች የሚዳርግ (ከነፃ ውድድር ሊገኝ የሚችል የዋጋ ቅናሽን በማሳጣት) ከመሆኑም ባሻገር የግዥ ዕቅዶች ክፍተት እንዳለባቸው አመላካች በመሆናቸው የሙስና ስጋቶች ተብለው ሊወሰዱ ይችላል፡፡
- በዘርፉ አብዛኛው ተቋማት ግዥ ሲከናወን በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ ለተጋነነ የምርቶች/አገልግሎቶች ዋጋ ስለሚጋብዝ የሙስና ስጋት ነው፡፡

## በዘርፉ የሚታየዉ የኦዲት ግኝቶች

- በግብርና ሚኒስቴር ለተለያዩ ቅድመ-ክፍያዎች የተከፈለና ያልተወራረደ ሂሳብ ብር 92,025,585.57፣
- የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት ለግንባታ ስራ ተቋራጭ፣ ለደመወዝ፣ ወዘተ ከተከፈሉ ቅድመ-ክፍያዎች ውስጥ ያልተወራረደ ብር 45,248,502.63 (የውስጥ ኦዲት)/ ብር 42,870,851.04 (የውጭ ኦዲት)፣
- በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ከቅድመ-ክፍያ፣ ከስራ ማስጀመሪያ እና ከሌሎች ያልተወራረደ ብር 1,489,401.50፣
- የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ለፕሮጀክት ከወጣ ወጪ ያልተወራረደ ብር 36,411,274.58 (የውስጥ ኦዲት)/ ብር 40,850,865.91 (የውጭ ኦዲት)፣
- የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ከአምስት ድርጅቶች ያልተወራረደ ብር 2,103,422.97፣
- የኢትዮጵያ ደን ልማት ከግንባታ ቅድመ-ክፍያ እና ከልዩ ልዩ ክፍያዎች ያልተወራረደ ብር 136,110,314.04፣
- የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ከኮንትራት-ቅድመ ክፍያ ያልተወራረደ ብር 168,638.31 (የውስጥ ኦዲት)/ ብር 165,507.69 (የውጭ ኦዲት)፣
- በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በውጪ ኦዲት የተገኘ ያልተወራረደ ሂሳብ ብር 6,270,596.33 እንዲሁም በውስጥ ኦዲት የተገኘ ለምን ስራ እንደሆነ በግልጽ ባልታወቀ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦ የተገኘ ብር 284,080.11፣

### 2.7.3.2. የፕሮጀክት ፈንድ አጠቃቀም (the use of project funds)

ሥነምግባር በጎደላቸዉ ባለሥልጣናቱ ለግብርና ልማት የሚውሉ የፕሮጀክት ገንዘቦችን ወደ የግል ሒሳቦች ወይም ከግብርና ላልሆኑ ፕሮጀክቶች ማዛወር ይችላሉ። ይህ አላግባብ ምዝበራ የግብርና ጅምርን የታሰበውን ጥቅም በእጅጉ ያደናቅፋል። ሙስና ሊገለጽ የሚችለው የተጋነነ የኮንትራት ስምምነቶችን በመጠቀም ቃላቸውን ለማያሟሉ ወይም ደረጃቸውን ያልጠበቁ እቃዎችና አገልግሎቶችን ለሚያቀርቡ ኩባንያዎች ነው። ይህም ብዙ ጊዜ የሀብት ብክነት እና በቂ ያልሆነ የግብርና ግብአቶች ያስከትላል። ሥነምግባር በጎደላቸዉ የመንግስት ባለሥልጣኖች ሀብቶችን፣ ፈቃዶችን ወይም የፕሮጀክት ኮንትራቶችን ለመመደብ ጉቦ ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህ አሰራር ወደ ዝቅተኛ የፕሮጀክት ውጤቶች ሊያመራ ይችላል። አንዳንድ ገንዘቦች ላልነበሩ ወይም ጨርሰው ላልተተገበሩ "የ ghost ፕሮጀክቶች" ሊመደብ ይችላል። ይህ አሰራር ምንም አይነት ትክክለኛ የግብርና ልማት ሳያስገኝ የህዝብን ሃብት ይዘርፋል።

በቂ ያልሆነ የክትትል እና የግምገማ ዘዴዎች ቁጥጥር ወደሌለው ሙስና ሊመራ ይችላል፣ ምክንያቱም የፕሮጀክት ፈንዶች እንዴት እንደሚወጡ በቂ ተጠያቂነት ሊኖር ይችላል። ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍል ብልሹ አሰራር ሊፈጠር። የመሬት ድልድል ሂደት ሥነምግባር የጎደላቸዉ ባለስልጣኖች ሥልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ለግል ባለሀብቶች በአገር ውስጥ አርሶ አደሮች እና ማህበረሰቦች ወጪ መሬት ሲሰጡ ሙስና ይታያል። የውሃ እና መሬትን ጨምሮ የግብርና ሃብቶችን በአግባቡ አለመጠቀም በተለያዩ ደረጃዎች ሙስና ሊባባስ ስለሚችል ለውጤታማነት ጉድለት እና የግብርና ምርትን ይቀንሳል።

**በዘርፉ አየተከናወኑ ካሉ ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ**

- በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ (የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች መካከል microscopic organs እና እንስሳት ላቦራቶሪ ግንባታ ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቁ ብር 13,343,263.30 መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲጋለጥ ያደረገ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ውስጥ አምስቱ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣ የግብርና ሚኒስቴር እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁት ብር 10,730,215.03 መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲጋለጥ ያደረጉ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ደን ልማት እያስገነባቸው የሚገኙ ሁለት የደን ምርምር ማዕከላት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣

- ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸው (የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት የደቂቅ አካላትና እንስሳት ላቦራቶሪ ግንባታ ፕሮጀክት ብር 28,226,001.24 ተጨማሪ ስራ የተሰጠበት፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች በሶስቱ ላይ ተጨማሪ ስራ በብር 2,625,255.29 የተሰጠበት ሁኔታ፣ የግብርና ሚኒስቴር እያስገነባቸው ከሚገኙ የፕሮጀክት 66,980,025.06 ብር ተጨማሪ ስራ የተሰጠበት፣

- የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት (የግብርና ትራንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች 10 የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት ግንባታ ተጨማሪ 104 ሚሊዮን ብር የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት መሆኑ)፣

- ውል የተቋረጠባቸው እና ተቋራጩ ክስ የተመሰረተበት (የኢትዮጵያ ብዝሀ-ህይወት ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ተቋራጩ የጠፋበት/ውል የተቋረጠበት የፍቼ ዱፕሊኬቲንግ ጂን ባንክ ግንባታ እንዲሁም ተቋራጩ የተከሰሰበት የባህርዳር ዙሪያ ሜጫና ወንዳጣ ፕሮጀክት፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እያስገነባቸው ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ዘጠኙ ላይ ውል የተቋረጠ መሆኑ፣ አንድ ተቋራጭ ላይ ክስ የተመሰረተበት እንዲሁም አንድ ተቋራጭ በኢንስትቲዩቱ ላይ ክስ የመሰረተበት መሆኑ)፣

- የዋጋ ማስተካከያ በተለያዩ ግንባታዎች ላይ የሚሰጥበት አሰራር ከዕቃዎች የዋጋ መናር አንፃር የመነጨ ሊሆን ቢችልም፣ ከአላግባብ የጥቅም ግንኙነት ጋር ተያይዞ የመምጣት ዕድል ሊኖረው ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው ብሎ መደምደም ይቻላል::

**ማጠቃለያ ጥያቄዎች**

1. በግብርና ምርት የዕሴት ሰንሰለቶች ዉስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን የሙስና አደጋዉች/ተጋላጭነት ምንድን ናቸው?
2. በግብረናዉ ዘርፍ ከጊዢ እና ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚታዩ የስነምግባርና የሙስና ችግሮች ላይ ይወያዩ:: በምን መንገድ መቀነስ እንደሚቻል ሃሳብ ይስጡ?

## ማጠቃለያ

*በዚህ ክፍል ግብርና ዘርፍ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ እና ለኢንዱስትሪው ዘርፍ መሰረታዊ ጥሬ ዕቃዎችን በማቅረብ የኢኮኖሚ መሰረት መሆኑን፤ እንዲሁም በግብርናው ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና ከፍተኛ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል፤ በተለይ አብዛኛው ሕዝብ ግብርናን ዋና መተዳደሪያ በደረገባቸው በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ተጽእኖው የበለጠ ከባድ ሊሆን እንደሚችል ለማሳየት ተሞክረል። በተጨማሪም በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ግብርና በዋናነት የሚከናወነዉ በጥቃቅንና አነስተኛ እንዲሁም መሬት በሌላቸው ገበሬዎች ሲሆን ባጠቃላይ የአቅም እና የካፒታል ችግር ያለባቸው እና ድምጽ በሌላቸው ገበሬዎች በመሆኑ ችግሩን የጎላ እንደሚያደርገዉ ተነስተል። አብዛኛዎቹ የግብርና እሴት ሰንሰለቶች ያላቸዉን አምስት ደረጃዎች ማለትም ግብአት (መሬት፣ዉሃ፣የእርሻ ግበዓቶች) ምርት፣ ሂደት እና ማሸግ፣ ማከማቻና ስርጭት እና የመጨረሻ ገበያዎች ተተነትኖዋል። የግብርና መሰረታዊ የእሴት ሰንሰለት መዋቅርን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሙስናን አደጋዎች በየደረጃዉ ለማየት ተሞክረል። በግብርናዉ ዘርፍ ሙስናን ለመዋጋት ወይም ለመመርመር የእሴት ሰንሰለቱን መከተል አንድ አካሄድ ቢሆንም፤ ዉስብስብ ከሆነዉ የሙስና በኒሪ አንጻር በተለየ መንገድ መመልከት እንደሚገባ ተብራረተል። ስለዚህም በዘርፉ የሚፈጸሙ ግዢዉች፣ በሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ላይ እና በሚንስቴሩ እና በተጠሪ ተቃሞች ዉሰጥ የሚታዩ የኦዲት ግኝቶች እና ሌሎች የተጋላጭነት ሁኔታዎች ተብራራቱዋል፤ እንዲሁም የግብርናውን ዘርፍ ለሙስና እና ለመልካም አስተዳደር ችግር የሚያጋልጡ ጉዳዮች በዝርዝር ተዳሱል።*

# ምዕራፍ ሶስት

## ሙስና በግብርና ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት እና መከላከያ ስልቶች

### 3.1. መግቢያ

ሙስና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያጠቃና የተንሰራፋ ጉዳይ ሲሆን በተለይ በግብርናው ዘርፍ ላይ ያለው ተጽእኖ ከፍተኛ ነው፡፡ በብዙ ታዳጊ ሀገራት ግብርና የኢኮኖሚው ወሳኝ አካል ሲሆን ለአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል መተዳደሪያ እና ለምግብ ዋስትና አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ሙስና የግብርና ስርአቶችን ቅልጥፍና እና ውጤታማነት ሊያሳጣው ይችላል፣ በአርሶ አደሩ፣ በተጠቃሚው እና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ውጤቶችን ያስከትላል፡፡ ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል፡፡

### 3.2. የምእራፉ ዓላማ

**ከዚህ ምእራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-**

- ሙስና በግብርናዉ ዘረፍ የሚያስከትሉት ጉዳትጉዳቶች እና ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያለዉን ተጽእኖ ይዘረዝራሉ፤
- ሙስና በዘርፉ ላይ ያለዉን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፤
- ብልሹ አሰራርን ተከትሎ የግብርና ምርትና ስርጭት ቅልጥፍናን በመለየት በዘርፉ የተሻሻሉ የአሰራር ዘዴዎችን ይነድፋሉ፡፡
- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
- በዘርፋቸው የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ፣

### 3.3. የተፈቀደው ሰዓት

ይህን ምእራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 6:00 ሰዓት

## 3.4. ሙስና በግብርና ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት (Impact of Corruption in Agriculture)

### *3.4.1. ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች (Economic impacts)*

ለተወሰኑ የዘርፍ ምርቶች በተለይም የግብርና ዘርፍ የዋጋ መጨመር የሚያስከትለው መዘዝ በ Njegovan and Tomaš-Simin (2020) ጥናት ተደርጎበታል፣ ይህም የአምራች ዋጋ ኢንዴክስ መጨመር የግብርና ክሬዲቶችን አያያዝ ላይ አድኣዊ ያደርገዋል:: Therefore, debtors want to make a profit because the money used to pay off the debt is worth less than when the debt was valued. In turn, the lenders of such agricultural loans will see the real value of their credit decrease.

ሌላው የግብርና የዋጋ ንረት ውጤት በአንደኛ ደረጃ ዘርፍ የሚመነጨ የተወሰኑ የገቢ ክፍሎችን የመግዛት አቅምን መቀነስ ማለትም የተወሰኑ ሰራተኞች እና ባለሀብቶች በግብርና ምርቶች የሚደገፉ የገቢ መጠን እና ዋጋቸው ቀስ በቀስ እየተሻሻለ ነው:: የግብርና ምርቶች ከፍተኛ ዋጋ ካለባት ሀገር በሌሎች ሀገራት ከሚመረቱ ተመሳሳይ ምርቶች ጋር ሲነፃፀሩ በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነትን የማጣት ስጋት አለባቸው:: በዚህ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ባለባቸው አገሮች የግብርና ምርቶች አምራቾች የትርፍ መጠን ይቀንሷል:: ይህም ከእነዚህ ዘርፎች ወደ ሌሎች በሀገሪቱ ውስጥ ወደሚገኙ ተወዳዳሪ ዘርፎች ኢንቨስትመንቶች እንዲወጡ ሊያደርግ ይችላል::

የግብርና ዘርፍ በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ካለው ክብደት አንፃር ሲታይ፣ በግብርናው ዘርፍ ያለው የዋጋ ንረት የአገሪቱን ዓለም አቀፍ የወጪ ንግድ መቀነስ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች መጨመር እና የብሔራዊ ምንዛሪ መዳከም ዝንባሌን ያስከትላል (Reding 1996):: በአጠቃላይ ሙስና ለገበሬዎች ተጨማሪ ወጭ ይጨምራል፣ እና ስለዚህ የጥላ ዋጋ የግብዓት ዋጋ (ማለትም production input) ይጨምራል:: ከፍተኛ ዋጋ ወይም ወጭ ደግሞ ገበሬዎችን ብዙ ግብአቶችን እንዳይጠቀሙ ይገድባል:: በመንግስት ባለስልጣናት እና በግሉ ሴክተር ድርጅቶች መካከል ያለው ትብብር፣ ለምሳሌ የመንግሥት ሠራተኛ ሥልጣኑን ተጠቅሞ ማዳበሪያውን በውድ ዋጋ ለመሸጥ ወይም በጠቅላላ ለገበሬው ለማሰራጨት የታሰበዉን ግብዓት መጠን በመቀነስ ገበሬዎችን ለተጨማሪ የግብዓት ወጪ ማጋለጥ ይችላል::

**ኬዝ 7. የግብርና ግብአቶች ሙስና (ማዳበሪያ፣ ዘር)**

የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት

ገጽ 31<br>የምዝገባ ቁጥር 63717<br>ቀን 21/08/2016<br>ሰዓት 10:30

በዚህ የሙስና ወንጀል የቀድሞ የጎማ ወረዳ ግብርና ሰራተኛ የነበሩት አቶ ከድር አ/ታማም በተከሰሱበት ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቷል። የሙስና ወንጀል ህግ ቁጥር 881/2 አንቀጽ **31(2)**ን በመተላለፍ የተፈፀመ እምነት መጣስ ከባድ ወንጀል ነው። ተከሳሹ ከቀን 01/07/2023 ጀምሮ በጅማ ዞን ቡልቡሎ መንደር፣ ጎማ አውራጃ በሚገኘው ዳራርቱ ካታ ሙዱጋ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር መጋዘን ሰራተኛ ሆኖ ይሰራ ነበር። ከ10/07/2023 እስከ 21/04/2016 ባለው ጊዜ ውስጥ WHG Qonna Maraa Coocee Guddaa ላይ በተደረገ ኦዲት የተለያዩ ማዳበሪያ NPSB መደበኛ 6 (ስድስት) ኩንታል ዋጋው 23,716.02 (ሃያ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ አሥራ ስድስት ከ ሁለት ሳንቲም)፣ 6 ( ስድስት) ኩንታል ዩሪያ ማዳበሪያ፣ ዋጋው 23,397.42 (ሃያ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና ሰባት ከአርባ ሁለት ሳንቲም)፣ 5.825 ኩንታል የ ሊሙ በቆሎ ዘር፣ ዋጋው 88,307 (ሰማንያ ስምንት ሺህ ሦስት መቶ ሰባት)፣ B546 የበቆሎ ዘር፣ 10.25 ሺህ ኩንታል፣ 60,485.25 (ለስል ሳሺህ አራት መቶ ስምንት ከሃያ አምስት ሳንቲም) በአጠቃላይ ብር 195,905.69 (አንድ መቶ ዘጠና አምስት ሺ. ዘጠኝ መቶ አምስት ከ ስልሳ ዘጠኝሳንቲም) በመቀነስ የእምነት ጥሰት ተከሷል። የጅማ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወንጀል ቀን 21/08/2016 በዋለ ችሎት የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል። ስለሆነም የከሳሽ የዳራርቱ ካታ ሙዱጋ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበርን ንብረት፣ ከማዳበሪያና በቆሎ ዘር 216 ብር ከ375.69 ሳንቲም የሙስና ወንጀሎች ህግ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ **31(2)** እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት አንቀፅ 149(5) የወንጀሉን ሁኔታ፣ የወንጀሉን ከባድነት፣ የአቃቤ ህግ ምግባር አደገኛነት እና የተከሳሹን የትምህርት ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በአራት (4) አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል። ከተያዘበት ቀን ጀምሮ እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 90(2) መሰረት የገቢ ምንጭን እና የተከሳሹን ቤተሰብ የማስተዳደር ሃላፊነት ግምት ውስጥ በማስገባት ተከሳሹ በሶስት ሺህ (3000) ብር እንዲቀጣ በሙሉ ድምፅ ትእዛዝ ወስነናል።

**መልመጃ 3.1**

በግብርናው ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና ሰፊ ኢኮኖሚያዊ መዘዞች የሚያስከትል መሆኑ ግልጽ ነዉ። እነዚህን እውነታዎች በተመለከተ እባክዎ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፣

- ✓ ሙስና የግብርና ምርታማነትን እንዴት ይጎዳል?
- ✓ ሙስና በግብርና ልማት ኢንቨስትመንት ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?
- ✓ ሙስና በግብርና ላይ የህዝብ ወጪን የሚጎዳው በምን መንገዶች ነው?
- ✓ በግብርናው ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና የረዥም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ መዘዞች ምንድናቸው?

### *3.4.2. የአካባቢ መበላሸት (Environmental degradation)*

በትርጓሜው፣ ሙስና ለግል ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም ነው (Werlin, 2016)፡፡ ነገር ግን፣ ሙስና እንደ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ወረርሽኝ የምንኖርበት ዓለም የአካባቢ ዘላቂነት እና ጥራት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፣ የአየር ንብረት ለውጥ አሁንም ሆነ ወደፊት ህልውናችንን አደጋ ላይ ይጥላል (Lisciandra & Migliardo, 2017)፡፡ ሙስና የአካባቢ ጥበቃ ደንቦችን እና ፖሊሲዎችን ጥብቅነት በማዳከም የተፈጥሮ ሀብትን በብቃት መጠቀም ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ Lack of or weak environmental laws lead to inefficient use of natural resources and ultimately environmental degradation (Wang et al., 2019; Zhou & Li, 2021)፡፡ ሙስና የአካባቢ ጥበቃ ደንቦችን ከማዳከም በተጨማሪ አንድ ሀገር አረንጓዴ እነዳትሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ገቢ መቀነስ፣ የአስተዳደር ጉድለት፣ የመንግስት ትኩረት መቀየር እና ለአካባቢ ጥበቃ ፕሮጀክቶች ያለ አግባብ መጠቀምን ያመጣል (Ren et al., 2021b)፡፡ በእርሻ ላይ ያለው ሙስና ጎጂ የሆኑ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን፣ ማዳበሪያዎችን እና ሌሎች ኬሚካሎችን መጠቀም በአርሶ አደሩ፣ በተጠቃሚው እና በአካባቢው ላይ አሉታዊ የግብርና ችግሮች ሊያስከትል ይችላል፡፡ እነዚህን ኬሚካሎች መጠቀም እንደ ካንሰር፣ የልደት ጉድለቶች እና የነርቭ በሽታዎች ያሉ የግብርና እክሎችን ያስከትላል፡፡

**መልመጃ 3.2**

በግብርናው ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና ሰፊ የአካባቢ መበላሸት መዘዞች የሚያስከትል መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ እነዚህን እውነታዎች በተመለከተ እባክዎ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፣

- ✓ በግብርናው ዘርፍ ለአካባቢ ጉዳት የሚያበረክቱ ዋና ዋና የሙስና ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
- ✓ በግብርና የሚታዩ ሙስናዎች የአካባቢ ጥበቃ ደንቦችን ማስፈጸም ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያሳድራል?

- ✓ ማዳበሪያና ፀረ ተባይ ኬሚካል ስርጭቱ ብልሹ አሰራር ለአፈርና ለውሃ ብክለት አስተዋጽኦ የሚያደርገው እንዴት ነው?
- ✓ አካባቢን ለመጠበቅ በግብርናው ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናዎችን ለመከታተልና ለመዋጋት ምን ዓይነት ዘዴዎችን መዘርጋት ይቻላል?

### *3.4.3. ማህበራዊ አንድምታ (Social implications)*

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች** (Brainstorming questions):

- ✓ የግብርና ሙስና የማህበራዊ እኩልነትን የሚያባብሰው፣በተለይ የተገለሉ እንደ አነስተኛ ገበሬዎች፣ሴቶች እና ተወላጆች ማህበረሰቦች በየትኞቹ መንገዶች ነው?
- ✓ ለአነስተኛ ገበሬዎች ከትላልቅ የግብርና ንግዶች ጋር ሲነፃፀር ሙስና የግብርና ሀብት (እንደ መሬት፣ ውሃ እና ብድር) አቅርቦት ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?

በሶሺዮሎጂ እይታ ሙስና የተዛባ ባህሪ መገለጫ ነው፣ የጋራ መመዘኛዎችን ችላ ማለት፣ ከግለሰቦች የሚፈለጉትን አለመቀበል፣ ከመደበኛ ግዴታዎች እና ደንቦች ያፈነገጠ ነው። ብዙ ጊዜ፣ የሙስና ምክንያት የገንዘብ ጥቅም ነው፣ ምንም እንኳን ሌላ ቁሳዊ ወይም ቁሳዊ ያልሆነ ጥቅም፣ ለምሳሌ የፖለቲካ ካፒታል ወይም ሌሎች ልዩ ጉዳዮች ብገኙም።

የተወሰኑ የሙስና ዓይነቶች መከሰት ከአካባቢው ጥሩ የመራቢያ ቦታ እና ለሙስና ሁኔታዎችን ከማቅረብ ጋር በቅርበት የተያያዘ ነው። ሙስና በተለይም በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች፣ የገንዘብ ድልድል፣ የህዝብ ግዥዎች፣ ተወዳዳሪ ጨረታዎች፣ የመንግስት ውሎችን ሲሰጡ፣ የመንግስት ንብረትን ማስተላለፍ፣ ድጎማዎችን መስጠት፣ ብልሹ ባህሪ እንደ ውስብስብ ማህበራዊ ግንኙነት እና አካላት እና ተቋማት ውድቀት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሙስና የሚፈጠረው ህጎች፣ የቁጥጥር ስርዓቶች እና መደበኛ ያልሆኑ ማህበራዊ ህጎች ብልሹ ባህሪን ሲያደርጉ ወይም ችላ ሲሉ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። ብልሹ ባህሪን ከመቅጣት ይልቅ በዘዴ የመደገፍ ሁኔታዎች፣ የበለጠ እንዲስፋፋ ያበረታታሉ። እንደዚህ ባሉ ጉዳዮች ላይ አስተዳዳሪዎች ያለ ህጋዊ መብት መብትን ለማሸነፍ፣ የማህበራዊ ፍትህ ጥሰት፣ የማህበራዊ ግንኙነቶችን አለመረጋጋት እና በተለይም በህብረተሰቡ ውስጥ የሞራል እሴቶችን መበሰበሰን በሚመለከቱበት ጊዜ አስተዳዳሪዎች ጉድለቶችን ማጣት ይጀምራሉ።

የሙስና ድባብ የሚፈጠረው በዜጎች ማለትም የሙስና ምልክቶችን ቸልተኛ በመሆን ነው። አሁን ያለው ህብረተሰብ የቁሳቁስ እሴቶቹ የትኩረት ማዕከል ሆነው የስነ-ምግባር እና የታማኝነት

ገጽታዎች ላይ በማተኮር በግለሰብ ነፃነት ላይ የማተኮር ዝንባሌ አላቸው። ለሙስና ባህሪ በቂ ያልሆነ ማህበራዊ መቻቻል፣ ያለውን ብልሹ ባህሪ ሪፖርት ለማድረግ እና በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ ምስክርነት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ነው። በአጠቃላይ በሕዝብ ጉዳዮች አስተዳደር ውስጥ ለመሳተፍ ያለው ፍላጎት አነስተኛ ነው።

### 3.4.4. ለአስተዳደር እንድምታ (Implications for management)

የመንግስት ተቋማት ደካማ በሆነባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ሙስና እየሰፋ ነው። ረሃብን በስርዓት ለመዋጋት አለም አቀፍ እና ክልላዊ የልማት ተቋማት በሚያደርጓቸው ሙከራዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በመፍጠር ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ይከለክላል። የገበያ ሥራዎችን ያዛባል። ምንም አይነት ተነሳሽነት በምግብ ዋስትናም ሆነ በድህነት ቅነሳ ወይም በሌላ ማንኛውም ነገር በመልካም አስተዳደር ባህል ምክንያት የስነምግባር ህዝባዊ ባህሪ ከሌለ አይሰራም። ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በስተደቡብ ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ከመጠን በላይ መጨመር እና የተለያዩ የሙስና ዓይነቶች በአህጉሪቱ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦችን (Millennium development goals) ለማሳካት የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የሚያደርሱትን ተፅእኖ አደጋ ላይ ይጥላሉ። ከተቋማዊ አለመረጋጋት አንጻር የመሬት ይዞታና የውሃ አስተዳደርን ጨምሮ ትክክለኛ የረጅም ጊዜ የግብርና ፖሊሲዎችን በማውጣትና በመተግበር ሙሰኛ መንግስታት ሊጠበቁ አይችሉም።

### 3.4.5. የምግብ ዋስትና ስጋቶች (Food security concerns)

ሙስና ረሃብን በስርዓት ለመዋጋት አለም አቀፍ እና ክልላዊ የልማት ተቋማት በሚያደርጓቸው ሙከራዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በመፍጠር ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ይከለክላል። ኢትዮጵያን ጨምሮ በታዳጊ አገሮች ሙስና በግብርና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት በዋናነት በሁለት ዘርፎች ይታያል፡- አንደኛ፣ የግብርና ምርቶች ስርጭት። በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተመረተ ያለው የምግብ መጠን ዓለምን ለመመገብ በቂ እንደሆነ በጥናት ተረጋግጧል። But international trade and intellectual property regulations undermine the distribution of these products to vulnerable groups, often smallholder farmers and women in developing countries. የአካባቢው አርሶ አደሮች የተሻሻሉ ዝርያዎችን እና ምርትን ለመጨመር የሚያስፈልጉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና ዘር ማግኘት አይችሉም ምክንያቱም የእነዚህ ምርቶች ዋጋ ከፍ ያለ በIP (intellectual property) እና የንግድ ስምምነቶች ምዕራባዊ ሞኖፖሊዎችን የሚደግፉ ናቸው። እነዚህ ስምምነቶች የተፈረሙት በአፍሪካ ሀገራት መንግስታት ፈቃድ ነው። በሁለተኛ ደረጃ፣

የወቅቱ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት እና የአይ.ፒ. ህጎች ይዘቶች የሚወሰኑት በትልልቅ የግል ንግዶች እና ትልቅ ኢኮኖሚ ባላቸው አገሮች ነው። የእነዚያ ሀገራት መንግስታት የዜጎቻቸውን የምግብ ዋስትና ፍላጎት ለማሟለት የመረጡት ለአጭር ጊዜ የውጭ ኩባንያዎች ክፍያ ነው። ሙስና በተለያዩ እርከኖች የሚከሰት ሲሆን አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመግታት የሚደረገው ጥረት በግብርናው ዘርፍ ሙስናን የሚያመቻቹ ተጨባጭ የህግ፣ የአሰራር፣ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን የሚሸፍን ዘርፈ ብዙ እርምጃ ያስፈልገዋል።

ሙስና በተለያዩ መንገዶች የምግብ ዋስትና እጦትን ሊያባብስ ይችላል። For example, by damaging food availability because households have to spend money on bribes or else be selected for food. ሙስና ለገበሬዎች ተጨማሪ ወጪን ስለሚጨምር የጥላ ዋጋ (ማለትም የግብዓት ግዥ) ይጨምራል። ከፍተኛ ዋጋ ወይም ወጭ ገበሬዎችን ብዙ ግብአቶችን እንዳይጠቀም ይገድባል። ይህም ከፍተኛ የምርት ቅነሳን ያስከትላል። ወቅታዊ የምግብ ችግር በተለያየ መልኩ የሚፈጠሩ በርካታ የሙስና አደጋዎች አሉ። በምግብ እሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ነጥቦች፣ እንደ የምግብ ምርቱ ባህሪም ይወሰናል እንደ ምርቱ፣ ማከማቻ፣ ስርጭት እና አቅርቦት አውድ። የመንግስት ድጎማ እና እርዳታ መርሃ ግብሮችም ጠቃሚ የሆኑ የሙስና አደጋዎች የተቸገሩትን መድረስ ለምሳሌ፣ሴቶች፣ ድሆች እና ሌሎች የተገለሉ ህዝቦች ናቸው። በተመጣጣኝ ሁኔታ በምግብ ቀውስ እና በማንኛውም የፀረ-ሙስና ስትራቴጂ በምግብ ዋስትና ላይ ያተኮሩ ልዩ ፍላጎቶቻቸውን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። በአጠቃላይ በግብርና ላይ የሚስተዋለው ሙስና ለምግብ ዋስትና እጦት ያጋልጧል ምክንያቱም የምግብ አቅርቦትን ወደ ሌላ አቅጣጫ መቀየር፣ የዋጋ አጠቃቀምን እና የሃብት ክፍፍልን እኩል አለመሆን ያስከትላል። ይህ እንደ ድሆች፣ ህጻናት እና አዛውንቶች ባሉ ተጋላጭ ህዝቦች ላይ አስከፊ ተጽእኖ ይኖረዋል። የምግብ ዋስትና ማጣት ለተመጣጠነ ምግብ እጥረት፣ ለረሃብ አልፎ ተርፎም ለሞት ሊዳርግ ይችላል።

**መልመጃ 3.3**

በግብርናው ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና ሰፊ የfood security መዘዞች የሚያስከትሉ መሆናቸዉ ያልተደበቀ እውነት ነዉ። እነዚህን እውነታዎች በተመለከተ እባክዎ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

- ✓ ሙስና በምግብ ዋስትና ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምንድን ነው?
- ✓ ሙስና የገበሬውን ኑሮ የሚጎዳው እንዴት ነው?

✓ በእርሻ ላይ ሙስናን በተሳካ ሁኔታ ከቀነሱ አገሮች ምን ትምህርት ማግኘት ይቻላል?

### *3.4.6. የአየር ንብረት አደጋ (Climate disaster)*

*ሙስና የአካባቢ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚደረገውን ጥረት በማዳከም የአየር ንብረት አደጋዎችን በማባባስ ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታል። ሙስና በአካባቢ አስተዳደር ውስጥ ሰርጎ ሲገባ ውጤታማ ያልሆኑ የአየር ንብረት ፖሊሲዎች፣ የሀብት ክፍፍል እና የመተዳደሪያ ደንቦችን በአግባቡ አለመተግበር ያስከትላል* (Taconi and Williams, 2020)። *እደ* Cartier 2021 *መሠረት ግን፣ በህገ-ወጥ መንገድ ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ የደን መሬቶችን ማግኘት በተለያዩ ሙሰኞች (እንደ የመንግስት ሰራተኞች፣ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ዳኞች እና የንግድ ባለቤቶች) መካከል የሚደረግ ትብብርን ይጨምራል። ለምሳሌ በምስራቃዊ የፔሩ ክልል፣ የደን መሬት በህገ ወጥ መንገድ ለእርሻ ስራ እንዲውል ተደርገዋል። ዘላቂ የግብርና ልምዶች የሙስና አተገባበር ላይም ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላሉ።* In southern Benin, for example, smallholder farmers' lack of trust in local government, stemming from perceptions of corruption, has led to challenges in implementing government-led climate change adaptation measures (Taconi and Williams, 2020)።

## 3.5. በግብርናው ዘርፍ የሚፈፀሙ ሙስና መከላከያ ስልቶች (Means of mitigating corruption in agricultural sector)

***የማነቃቂያ ጥያቄዎች***

1. *የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ።*
    1. *በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ።*
    2. *ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ።*

### *3.5.1. የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት*

*ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው። ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቀቀው ሊያውቁ ይገባል። ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል። በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባር*

ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

### 3.5.2. ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

#### 3.5.2.1. ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው፡፡ ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም፡፡

ዘርፎች በሴክተሩ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን  ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡ ግልጽነት የህዝብ መዳረሻን በመፍቀድ መንቃት አለበት፡፡  ለምሳሌ፣ በአልባኒያ፣ በአካባቢው መንግስታት በመጀመሪያ ምክር ቤት ማቅረብ አለባቸው እንዲኖራቸው የሚፈልጓቸውን ንብረቶች ዝርዝር ሚኒስትሮች ከሕዝብ መንግሥት ወደ ሥልጣናቸው ተላልፈዋል  (Zúñiga 2018)፡፡ ግልጽነት ለመጨመር ሌሎች መፍትሄዎች ለምሳሌ በቴክኖሎጂ የተደገፈ መፍትሄዎችን ያካተታ ሙስናን ለመከላከል ክፍት መረጃን ማስተዋወቅ፣ ሆኖም፣ እነዚህ ተነሳሽነቶች “መሠረት ያለባቸው መሆን አለባቸው” (Land Portal 2021)፡፡ የዩናይትድ ስቴትስ ኤጀንሲ ለ ዓለም አቀፍ ልማት (ዩኤስኤ አይዲ) በሙስና ላይ በግብርና ውስጥ ለመቃወም ጥረቶች ሙስና ግልጽነት፣ ግንዛቤ፣ ተጠያቂነት፣ መከላከል እና ማስፈጸም ላይ ማተኮር አለበት ይላል (Fink 2002)፡፡

#### 3.5.2.2. ተጠያቂነት

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው፡፡ ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራሀም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ

ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል።

**የኬዝ ትንተና IV**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ኬዞች በሚገባ በማጤን፡

- በየትኞቹ ኬዞች የስነምግባር ጉለት ታይቶባቸዋል፤የትኞቹስ ልክ ናቸዉ?
- ምን ምን ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች እንዳሉ በምክንያት በማስደገፍ ተወያዩባቸው
- ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች ያልታዩባችዉ ኬዞች ካሉ ምክኒያቶቹን ያስረዱ
- ኬዞቹን የሚያመሳስላቸዉ ነገር ይኖር ይሆን?

**ኬዝ 8. የማዳበሪያ ሙስና**

የግብዓት ማከማቻ እና ስርጭት አስተዳዳሪ አቶ ተፈራ ለማ የተባለ ግለሰብ የዋጋ ግምቱ ከ1 ሚሊየን ብር በላይ የሆነ 450 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በተሽከርካሪ በመጫን በግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ስም የተዘጋጀ ሀሰተኛ የወጪ ደረሰኝ በመጠቀም መነሻውን አዲስ አበባ በማድረግ ወደ አማራ ክልል በመዉሰድ በጥቁር ገበያ ዉሰጥ አንዱን ኩንታል እስከ 6000 ብር በመሸጥ ተጠቃሚ ሆነ።

**ኬዝ 9. የዶሮ እርባታ ሙስና**

በትንሽ ሴቶች የተቋቋመው አሰራር በስዋዚላንድ ውስጥ የዶሮ እርባታ ትብብር እንደ አንድ ምሳሌ ሆኖ ልያገለግላል ይቻላል። ለህብረት ሥራ ማህበሩ በሂደቱ ውስጥ ግልጽነት እና የመረጃ ተደራሽነት ስርዓት ለመቀላል የሂሳብ አያያዝ ዘዴ ነበር ጥቅም ላይ የዋለ። የግለሰብን ተጠያቂነት ለማስቻል እያንዳንዱ አባል መረጃ በመጽሐፍ ጠብቆ ወርሃዊ ሪፖርት የቀርባሉ። ባለድርሻ አካላት በነበሩበት ሁኔታ በሂሳብ አያያዝ ውስጥ ማንበብና መጻፍ የተገድቡ፣ እነሱ በልጆቻቸው ታግዘዋል። ስብሰባዎች በከፍተኛ የተሳትፎ መጠኖች መደበኛ ነበሩ። የኅብረት ሥራ ማህበሩ የቴክኒክ ድጋፍ እና ስልጠና ከግብርና ሚኒስቴር ወስዶዋል። ስለዚህ ግልጽነት በተከፈተ ተሳትፎ፣

ተደራሽነት እና መረጃ ተሰምነት ተቋቋመ:: **Source:** https://www.u4.no/publications/anti-corruption-measures-for-reducing-corruption-in-agriculture.pdf

**መልመጃ 3.4**

ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ማሳደግ የግብርና ሙስናን በመቀነስ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ እባኮትን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::

- ✓ በግብርና ተቋማት ውስጥ ያለው የግልጽነት ባህል በሙስና ደረጃ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?
- ✓ በመሬት ይዞታ እና በባለቤትነት ላይ ግልጽነት መጨመር የሙስና አደጋዎችን እንዴት ይቀንሳል?
- ✓ በግብርና ፖሊሲዎች ግልጽነት እና በሙስና መከሰት መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

### *3.5.3. የቅንነት ባህልን ማጎልበት*

በግብርናው ዘርፍ በሁሉም እርከኖች የሚስተዋሉ የሙስና አመራሮችን በሥነ ምግባር የታነፀ አመራርን ማሳደግ፣ እሴትን መሰረት ያደረጉ ውሳኔዎችን ማሳደግ እና ሙስናን መቻቻልን አለማክበር የታማኝነት እና የተጠያቂነት ባህል ለመፍጠር ያግዛል:: በማበረታቻዎች፣ ሽልማቶች እና እውቅናዎች የስነ-ምግባር ባህሪን ማበረታታት የፀረ-ሙስና ጥረቶችን ማጠናከር ይችላል:: እነዚህን እርምጃዎች በመተግበር እና በግብርና ላይ ሙስናን ለመከላከል አጠቃላይ አካሄድን በማስተዋወቅ፣ሀገራት እምነትን በማጎልበት የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማነት፣ፍትሃዊነት እና ዘላቂነት ማሻሻል ይችላሉ::

**መልመጃ 3.5**

- ✓ በተለያዩ ሀገራት የግብርና ሙስናን በመቀነስ ረገድ ምን ልዩ ማሻሻያዎች ተደርገዋል?
- ✓ በግብርናው ዘርፍ የሙስና ዋና ዋና ዘርፎች ምን ምን ናቸው? እና ማሻሻያዎች እነዚህን ችግሮች እንዴት ሊፈቱ ይችላሉ?
- ✓ በግብርና ላይ የሚደረገውን የድጎማ ስርጭት ማሻሻል የተዛባ አመዳደብ እና ብልሹ አሰራርን እንዴት ይከላከላል?

### *3.5.4. የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ*

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ (ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡ ፀረ-ሙስና ስልቶችን መዘርጋት እንደ ገለልተኛ የቁጥጥር አካላት፣ እንባ ጠባቂ ጽሕፈት ቤቶች፣ የመረጃ ጠላፊዎች ጥበቃ ዘዴዎች በግብርና ላይ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ያስችላል፡፡ በየጊዜው ኦዲት ማካሄድ፣ የሙስና ተግባራትን መመርመርና ለፍርድ ማቅረብ ሙስናን እንደማይታገስ ጠንካራ ማሳያ ነው:: የመሬት ይዞታን፣ የግብርና ግብአቶችን፣ ምርትን እና ግብይትን ጨምሮ የግብርና ሥራዎችን የሚቆጣጠሩትን ሁሉን አቀፍ ሕጎችና ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግና ሙስናን ለመከላከል ግልጽ መመሪያ በመስጠት ግለሰቦችና አካላት ለድርጊታቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡

### *3.5.5. የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ*

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

### *3.5.6. የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል*

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ የተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

### *3.5.7. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሜንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ*

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

**መልመጃ 3.6**

የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም የግብርና ሙስናን በመቀነስ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ እባኮትን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡

- ✓ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በግብርና ላይ የሚደረገውን ክትትልና ጥረት እንዴት ማሻሻል ይችላል?
- ✓ በግብርና ላይ የሚደርሰውን ሙስናን ለመዋጋት ዓለም አቀፍ አጋርነቶች የክትትል ማዕቀፎችን እንዴት ያጠናክራሉ?
- ✓ በግብርና ላይ ያለውን ሙስና የቀነሰውን የተሳካ የክትትል ስልቶችን የሚያቀርቡት ለየት ያሉ ጥናቶች የትኞቹ ናቸው?

### *3.5.8. የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር*

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቻ ሙሽናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- ➢ በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ➢ ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ➢ ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- ➢ የጥቅም ግጭትን የመከላከከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ➢ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- ➢ በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- ➢ በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

### *3.5.9. ትምህርት እና ስልጠና (Education and training)*

በግብርናው ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለድርሻ አካላት የስልጠናና የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮችን መስጠት ሙስናን ለመከላከልና የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ለማዳበር ያስችላል፡፡ የህዝብ ማሰልጠኛ ውጥኖች የገበሬዎችን፣ የግብርና ሰራተኞችን እና የባለስልጣኖችን ክህሎት እና እውቀት ሊያሳድጉ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ባለድርሻ አካላት ስለ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ ፖሊሲዎች እና ደንቦች ማስተማር መብቶቻቸውን እና ግዴታዎቻቸውን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፣ ይህም ብልሹ አሰራር ስር ሰዶ እንዳይሰራ ያደርገዋል፡፡ የሥልጠና መርሃ ግብሮች በግብርና ተግባራት ውስጥ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን አስፈላጊነት ሊያጎላ ይችላል፡፡ ባለድርሻ አካላት የእነዚህን መርሆዎች አስፈላጊነት

ሲረዱ ከእኩዮቻቸው እና ከባለሥልጣኖቻቸው ተጠያቂነትን የመጠየቅ እድላቸው ሰፊ ነው። ስልጠና ገበሬዎች እና የማህበረሰብ አባላት የግብርና ፖሊሲዎችን፣ የሀብት ድልድልን እና አስተዳደርን በሚመለከት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ እንዲሳተፉ ሊያበረታታ ይችላል። የተሳትፎ መጨመር የመንግስት እርምጃዎችን የበለጠ መመርመር፣ ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ይረዳል። ህዝባዊ ስልጠና በግብርናው ዘርፍ የመንግስት ባለስልጣናትን እና የግብርና ድርጅቶችን አቅም በማሳደግ ጠንካራ ተቋማትን ማዳበር ያስችላል። በደንብ የሰለጠኑ ሰራተኞች በሙስና ተግባር የመሳተፍ እድላቸው አነስተኛ ሲሆን የስነምግባር ደረጃዎችን የማክበር እድላቸው ሰፊ ነው።

### 3.5.10. ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው። ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል። እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል። አርሶ አደሮችን፣ ሲቪል ማኅበራትን፣ የግሉ ሴክተርን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በፖሊሲ አወጣጥ ሂደቶች ላይ ማሳተፍ በግብርና ላይ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ቁጥጥርን ለማሳደግ ያስችላል። የአስተያየት እና የቅሬታ ማስተናገጃ መንገዶችን መስጠት ባለድርሻ አካላት የሙስና ጉዳዮችን ሪፖርት እንዲያደርጉ እና ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላል።

### 3.5.11. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው። በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች**

<u>ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡</u>

- ብልሹ አሰራሮች በግብርና ምርታማነት እና ምርት ላይ የሚያደርሱት ኢኮኖሚያዊ መዘዞች ምንድናቸው?
- በግብርና ፖሊሲ ውስጥ ያለው ሙስና ወደ ዘላቂ ያልሆነ የግብርና አሠራር እንዴት ሊመራ ይችላል?
- በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኋቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት የትኖቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምንድን ነው?
- በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

**ማጠቃለያ**

*በግብርናው ላይ የሚስተዋለው ሙስና የሴክተሩን ውጤታማነት ይቀንሳል፣ ወጪን ይጨምራል፣ ምርታማነትን ይቀንሳል፣ ገበያን ያዛባል፣ አስተዳደርን ያዳክማል፣ የምግብ ዋስትና እጦትን ያባብሳል፣ ኢንቬስትመንትን ይከላከላል፣ የአካባቢ ጉዳትን ያስከትላል፣ ማህበራዊ እኩልነትን ይቀንሳል፣ በህብረተሰቡ ዘንድ መተማመንን ያጠፋል፡፡ እነዚህ ተፅዕኖዎች ዘላቂ ልማትን እና የግብርና ሥርዓቶችን የህዝብ ፍላጎት ለማሟላት እንዳይችሉ በጋራ እንቅፋት ይሆናሉ፡፡ ሙስናን መፍታት በዓለም አቀፍ ደረጃ የግብርና ሥርዓቶችን የመቋቋም እና ውጤታማነት ለማሳደግ ወሳኝ*

*ነው። መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው። ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው። በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም። ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አስራ አንድ ስትራቴጂዎች ተዘርዝሯል። ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ አስራ አንድ ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል። ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል።*

## 4. የ ቅድመ እና ድህረ ስልጠና ቼክ ሊስት (pre & post training Checklist)

በሰንጠረዥ ውስጥ የተቀመጡት የስልጠና ፌሬ ጉዳዮች ላይ ያላችሁን ግንዛቤና እና እውቀት በተቀመጡት ሃሳቦች ✓ ምልክት ያድርጉ።

| ተ/ቁ. | **የማረጋገጫ ዝርዝር** (Checklist) | ዝቅተኛ | ጥሩ | በጣም ጥሩ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለ ሙስና ጽንሰ ሐሳብ እና ፍቺ ግልጽ ግንዛቤ አለኝ | | | |
| 2. | መሰረታዊ የሙስና ዓይነቶችን መዘርዘር እችላለሁ | | | |
| 3. | በግብርና ውስጥ የተለመዱ የሙስና ዓይነቶችን መዘርዘር እችላለሁ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4. | አንድ ከፍተኛ ሥራ አስኪያጅ የፀረ-ሙስና ሕጉን የመተግበር ኃላፊነት የለበትም | | | |
| 5. | የድርጅትዎ ቦርድ እና ከፍተኛ አመራር ብዙውን ጊዜ ለግልጽነት እና ታማኝነት ምሳሌ ይሰጣሉ | | | |
| 6. | በድርጅትዎ ውስጥ ሰራተኞችን በመመልመል ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይከናወናል | | | |
| 7. | በግብርና ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ቅሌቶች የገጠር ልማትን እንዴት እንደሚጎዱ አውቃለሁ | | | |
| 8. | በመሬት ይዞታ ሂደት ውስጥ ያለው ሙስና ገበሬዎችን እንዴት እንደሚጎዳ ማብራራት እችላለሁ | | | |
| 9. | በግብርና አሰራር ላይ ሙስናን ለመዘገብ እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች መጥቀስ እችላለሁ | | | |
| 10. | ሙስና የምግብ ዋስትናን እና የግብርና ምርታማነትን እንዴት እንደሚጎዳ በግልፅ እችላለሁ | | | |
| 11. | ሙስና እንደ ዘርና ማዳበሪያ ያሉ የግብርና ግብአቶችን ተደራሽነት እንዴት እንደሚጎዳ በማብራራት እችላለሁ | | | |
| 12. | ሙስና በግብርና ምርምር እና በልማት ፈንድ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ለእኔ ግልጽ ነው | | | |
| 13. | በግብርናው ዘርፍ ያለው ሙስና የሚያስከትለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዘዞች ግልፅ ነው | | | |
| 14. | ከግብርና ጋር በተያያዙ ሙስና ውስጥ የመንግስት ድጎማዎች ሙስናን ለመቀነስ የሚጫወቱት ሚና ግልጽ ናቸው | | | |
| 15. | በግብርና አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዴት እንደሚሻሻል አውቃለሁ | | | |
| 16. | በግብርና ፖሊሲዎች ላይ የሚስተዋለውን ሙስናን ለመዋጋት ምን ዓይነት እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚቻል ግልጽ ሆኖልኛል | | | |
| 17. | የግብርና ሙስናን ለመቅረፍ የአለም አቀፍ ድርጅቶች ሚና በጣም ወሳኝ ነው | | | |
| 18. | ቴክኖሎጂ በግብርና ላይ ያለውን ሙስና ለመቀነስ የሚረዳው እንዴት እንደሆነ መዘርዘር እችላለሁ | | | |
| 19. | ሙስናን የመከላከል ዘዴዎች ለእኔ በጣም ግልጽ ናቸው | | | |
| 20. | ስለ ሙስና የተሻለ ግንዛቤ አለኝ | | | |

## 5. ዋቢ (References)

Anik, A. R., Manjunatha, A. V., & Bauer, S. 2013. Impact of farm-level corruption on the food security of households in Bangladesh. Food Security, 5(4), 565-574.

Baines, J. Open Democracy, Hager, B. S. 2021. Commodity trading: The shadowy industry destroying the planet. Equal Times.

Benjaminsen, T. A. and Ba, B. 2009. Farmer—herder conflicts, pastoral marginalisation and corruption: a case study from the inland Niger delta of Mali. The Geographical Journal.

Business Anti-Corruption Portal. 2017. Ethiopia Corruption Report.

Cartier, K. M. S. 2021. Climate change uproots global agriculture.

Cucagna, M. E., and Goldsmith, P. D. 2018. Value adding in the agri-food value chain. International Food and Agribusiness Management Association.

Dastrup, A., R. 2019. Introduction to human geography. Chapter 6.2. Press Books.

FAO. 2012b. Voluntary Guidelines on the Responsible Governance of Tenure of Land, Fisheries and Forests in the Context of National Food Security, Rome, Italy.

Farm Radio International. 2013. An introduction to agricultural value chains.

Fink, R. 2002. Corruption and the agricultural sector. Management Systems International and USAID.

Global Witness. 2013. Opaque structure of horsemeat company shows need for company reform.

Land Portal. 2021. Interview with Helena Vidalic from Transparency International on land corruption and open data.

Lawrence, F. 2011. The global food crisis: ABCD of food — how the multinationals dominate trade.

Lawrence, F. 2013. Horsemeat scandal: The essential guide. The Guardian.

Lindner, S. 2014. Ethiopia: Overview of Corruption in Land Administration. Transparency International.

Lisciandra, M., & Migliardo, C. 2017. An empirical study of the impact of corruption on environmental performance: Evidence from panel data. Environmental and Resource Economics, 68(2), 297—318.

Malak-Rawlikowska, A., Milczarek-Andrzejewska, D. and Fałkowski, J. 2019. Farmers' Bargaining.

Misra, A. 2020. Uttar Pradesh wakes up to Rs500 crore fertiliser scam. India Today.

Njegovan, Nikola, and Mirela Tomaš-Simin. 2020. Inflation and Prices of Agricultural Products. Economic Themes 58: 203—17.

Nkombo, N. 2018. Three ways the African Union can fight corruption in agriculture, and win.

Pearce, D. and Finckenstein, D. F. No date. Advancing subsidy reform: Towards a viable policy package. United Nations.

Puiuleţ, R., Bojin, D. and Radu, P. 2013. Offshore Secrecy: The horsemeat scandal. Organized Crime and Corruption Reporting Project (OCCRP).

Reding, Peter. 1996. Debt Crises and Exchange Crises. Papers 171. Paris: Notre-Dame de la Paix, Sciences Economiques et Sociales.

Ren, S., Hao, Y., & Wu, H. 2021b. Government corruption, market segmentation and renewable energy technology innovation: Evidence from China. Journal of Environmental Management, 300, 113686.

Rutledge, K., Costa, H., Sprout, E., Teng, S., McDaniel, M., Boudreau, D., Ramroop, T., Hunt, J. and Hall, H. 2011. The art and science of agriculture. National Geographic Encyclopaedia.

Schutter, O. E. 2016. Tainted lands: Corruption in large-scale land deals. International Corporate Accountability Roundtable (ICAR) and Global Witness.

Tacconi, L and Williams, D. A. 2020. Corruption and anti-corruption in environmental and resource management. Annual Review of Environment and Resources.

Transparency International. 2019. Rotten deals: How corruption spoils our food.

Van Hagen, I. 2021. Palm oil operations in Indonesia harm communities, foster corruption. Organized Crime and Corruption Reporting Project (OCCRP).

Wang, K., Yin, H., & Chen, Y. 2019. The effect of environmental regulation on air quality: A study of new ambient air quality standards in China. Journal of Cleaner Production, 215, 268—279.

Williams, A. 2021. Commodity supply chain traceability initiatives and their anti-corruption potential. World Wildlife Fund (WWF).

Werlin, H. H. (2016). Revisiting corruption: With a new definition. International Review of Administrative Sciences.

Westlake, M. 2005. Addressing marketing and processing constraints that inhibit agrifood exports. A guide for policy analysts and planners.

Zhou, A., & Li, J. 2021. Impact of anti-corruption and environmental regulation on the green development of China's manufacturing industry. Sustainable Production and Consumption, 27, 1944—1960.

Zúñiga, N. 2020. Gender sensitivity in corruption reporting and whistleblowing. Transparency International.

Zúñiga, N. 2018. Land corruption: Topic guide. Transparency International.

የተሻሻለው የፋዳራል የሥነምግባርና የጸረሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97.

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION
ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et